# ሥነ ፍጥረት




ሔኖክ ኢሳይያስ

Christo et Ecclesiae

# ማውጫ

ማውጫ ........ 3
መቅድም ........ 4
መግቢያ ........ 10
ምልከታ ........ 12
በመዠመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ ........ 13
ሥነ ሰብእ ........ 22
ርኩብ ........ 27
ሀልዎተ እግዚአብሔር ........ 29
ባሕርየ እግዚአብሔር ........ 32
መግበተ እግዚአብሔር ........ 38
የእኩይ ጣጣ ........ 42
ጥያቄ ........ 46
ስፍራ ........ 47
ጊዜ ........ 52
ዋቢ መጽሐፍት ........ 62

# መቅድም

ጥንታዊ ስያሜውን ተከትለን "ሥነ ፍጥረት" አልን እንጂ ትምህርቱስ በፍጥረታት መነሻነት የመለኮትን ነገር የምንማርበት ነው። ሥነ ፍጥረትን በአትኩሮት ስንመረምር መዳረሻችን እነርሱ ኾነው ሳይኾን በእነርሱ መነሻነት እግዚአብሔርን ለማወቅ ነው።[1] ወንድሜ አንባቢ ኾይ፤ እንግዲህ በፍጥረታት መነሻነት የፈጣሪን ነገር ለመማር ልቡናህን አዘጋጅ እንጂ ይህ መጽሐፍ የፍጥረታትን ነገር ግብ አድርጎ የተሰናዳ አይምሰልህ።

ሥነ ፍጥረት የቅዱሳት መጽሐፍትም ቀዳማዊ አስተምህሮ ነው። "ይኽ ስለ ምን ኾነ?" ቢባል፦ ሥነ ምግባር፣ ፍትሐ እግዚአብሔር፣ መግቦተ እግዚአብሔር፣ ትምህርተ ድኅነት፣ ነገረ ፍጻሜ... ወዘተ እኒህ ኹሉ በሥነ ፍጥረት ላይ የተመሠረቱ በመኾናቸው ነው። እኒህን ታላላቅ አስተምህሮዎች ለማወቅ አስቀድሞ ሥነ ፍጥረትን መርምሮ መረዳት ያስፈልጋል።

ሥነ ምግባር በሥነ ፍጥረት ላይ የተመሠረተ ነው ማለታችን፦ ቤተ እስራኤል "እታዘዘው ዘንድ እርሱ ማን ነው? ማንነቱን አላውቅም፤ ሕግጋቱን አልጠብቅም" እንዳይል፣ እግዚአብሔር ሕግጋትን ከመስጠቱ በፊት ኹሉን ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ የፈጠረ እርሱ መኾኑን በማስታወቁ ነው። ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ ፈጥሮናልና ሕግ ሊሰራልን ስልጣን አለው። የሕግ መምህር ሙሴ፣ ቅምረ ኮስሞስን[2] አስቀድሞ ሕግጋቱን ማስከተሉ፣ ዘፍጥረት የብሔረ ኦሪት ፊታውራሪ መኾኑ ለዚህ ነው። ሕግ የሠራልን እርሱ ሰማያትንና ምድርን በውስጣቸውም ያሉትን ኹሉ የሠራ በመኾኑ ልንታዘዘው ይገባል። ሕግን

---

[1] St. John Chrysostom, Homilies on Genesis, Homily 2.4: "From created things they might come to learn the architect of all and adore their maker, not stopping short at creatures"

[2] Cosmogony- የሥነ ፍጥረትን ጅማሮን የሚመለከት ትወራ።

የሚጠብቅ ሰው "የምድር ታማኝ ዜጋ- a loyal Cosmopolitan- ይኾናል" እንዳለ ይሁዲው ፊሎ።[3] ክቡር ዳዊት፣ "እጆችህ ሠሩኝ፤ አበጃጁኝ፤ ትእዛዛትህን እንድማር ማስተዋልን ስጠኝ"[4] ሲል የእግዚአብሔርን ፈጣሪነትና ሕግ ሠሪነት አቆራኝቶ መዘመሩ ለዚኽ ነው።[5] ዳግመኛም ፍትሐ እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረት ላይ የተመሠረተ ነው ማለታችን፦ የሠራውን ሕግ ቢጠብቁ ዋጋ የሚሰጥ፣ ባይጠብቁ የሚቀጣም እርሱ ራሱ በመኾኑ ነው።

መግቦተ እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረት ላይ የተመሠረተ ነው ማለታችን፦ መግቦት እግዚአብሔር ለሥነ ፍጥረት የሚወስደው ጥንቃቄ በመኾኑ ነው። "መገበ" ለማለት ፈጠረ ማለት ጥንቱ ነው። እግዚአብሔር በመፍጠር ያስገኘውን በመመገብ ያጸናዋል። ፈጥሮ ህልውና የሰጠውን፤ መግቦ ያጸናዋል። ሥነ ፍጥረትን በዓላማ ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ በመፍጠሩ እንጂ ፈጥሮትስ ባይኾን ባልተጠነቀቀለት ነበረ።[6]

ትምህርተ ድኅነት በሥነ ፍጥረት ላይ የተመሠረተ ነው ማለታችን፦ የሥነ ፍጥረት ሠራዒ እርሱ ስለኾነ ሥነ ፍጥረትን ሊያድስ መብት ያለው እርሱ ብቻ በመኾኑ ነው። : "Creation is the foundation of "all God's saving plans,"

---

[3] Philo, De Opificio Mundi, Sect. 1: "His (Moses') exordium, as I have said, is one that excites our admiration in the highest degree. It consists of an account of the creation of the world, implying that the world is in harmony with the Law, and the Law with the world, and that the man who observes the law is constituted thereby a loyal citizen of the world."

[4] መዝ 119፡73

[5] Moses Maimonides, The Guide of the Perplexed, Part 2, Chap. 27: "the belief in the production of the world is necessarily the foundation of the entire Law."

[6] Philo, De Opificio Mundi, Sect. 2: "For it stands to reason that what has been brought into existence should be cared for by its Father and Maker. For, as we know, it is a father's aim in regard of his offspring and an artificer's in regard of his handiwork to preserve them, and by every means to fend off from them aught that may entail loss or harm. He keenly desires to provide for them in every way all that is beneficial and to their advantage: but between that which has never been brought into being and one who is not its Maker no such tie is formed."

the “beginning of the history of salvation” that culminates in Christ.”[7] ድኅነትን በሚገባ ለመረዳት ውድቀትን መረዳት ያስፈልጋል፤ ውድቀትን ለመረዳት ከውድቀት በፊት የነበረውን አኗኗር መረዳት ያስፈልጋል።[8]

ነገረ ፍፃሜ በሥነ ፍጥረት ላይ የተመሠረተ ነው ማለታችን፡- ይኽን ዓለም ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ ፈጥሯልና ከመኖር ወዳለመኖር ሊያሳልፈው መብት ያለው እርሱ ብቻ በመኾኑ ነው።[9] እርሱ ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ ፈጥሯቸዋልና ሰማያትና ምድር በውስጣቸውም ያሉ ኹሉ የእርሱ ናቸው።[10] ጭቃው በሸክላ ሠሪው እጅ እንዳለ፣ ሥነ ፍጥረት ኹሉ በእግዚአብሔር እጅ ነው።

እግዚአብሔር ሰማያትንና ሠራዊታቸውን፣ ምድርንና በምድር ላይ በእግር የሚራመዱ፣ በክንፍ የሚበሩ፣ በባሕር የሚዋኙ እንስሳትን፣ ዕፀዋትን፣ አዝዕርትን፣ አትክልትንና "የፍጥረታት ዘውድ" የተባለው ሰውን ሲፈጥር ሰንብቶ፣ በሰባተኛይቱ ቀን ከሥራው ኹሉ ዐረፈ። እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ ስላረፈባት ይህች ዕለት "ታላቋ ሰንበት" ትባላለች።[11] እግዚአብሔር አምላካችን ከዐሥርቱ ቃላት አንዲቱ እርሷን አድርጎ፡- "እለተ ሰንበትን ቅዱስ አድርገህ አክብር"[12] ሲል አዟል። ሰንበት ”የአንድ ከተማ ሳይኾን፣ የአንድ ሐገር ሳይኾን የመላለሙ ክቡረ በዓል

---

[7] Catechism of the Catholic Church, Part 1, sect. 2, paragraph 4

[8] Hugh of St. Victor, De Sacramentis Christianae Fidei, Prologue: “It [Divine Scripture] first, at the very commencement of its narrative, recounts briefly and truthfully the beginning and constitution of the works of foundation. For it could not fittingly have shown how man was restored, unless it first explained how he had fallen; nor, indeed, could it fittingly have shown his fall unless it first explained in what condition he was constituted by God.“

[9] St. Basil, The Hexaemeron, Homily 1: “The dogmas of the end and of the renewing of the world are announced beforehand in these short words put at the head of the inspired history.”

[10] መዝ 89፡11

[11] ቀዳሚት ሰንበት- ዕለተ ቅዳሜ ናት፤ “ሰንበተ አይሁድ“ ትባላለች።

[12] ዘጸ 20፡8

ነው” እንዲል ፊሎ ዘእስክንድርያ።[13] በእለተ ሰንበት በሥነ ፍጥረት መነሻነት ፈጣሪ ይመለካል። ወንድሜ አንባቢ ሆይ፤ ሥነ ፍጥረት የአምልኮተ እግዚአብሔር መሠረት መኾኑን በዚህ ተረዳ!

እግዚአብሔር በነገሮች ላይ ያደረገው ቀዳሚ ክወና[14] ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ መፍጠር ነው። ይኽም ለሌሎች ክዋኔዎች መነሻና መሠረት ነው።[15] እግዚአብሔር ከሥነ ፍጥረት ጋር ያለውን ግንኙነት በፈጣሪነት ጀመረ። ፈጣሪነቱ ለገዢነቱ፣ ለመጋቢነቱ፣ ለአዳኝነቱ... ወዘተ ተቀዳሚ ነው። ታዲያ ዜና ፍጥረት የመለኮታዊ መገለጥ ፊት አውራሪ፣ የቅዱሳት መጽሐፍት የነገር መሪ ቢኾን ብርቱ ምንድን ነው? እምነቷ እንደ ቅዱሳት መጽሐፍት የኾነላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ጸሎተ ሃይማኖቷን “እኔ ኹሉን በሚችል ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ” ስትል ትጀምራለች።

ትዕይንተ ከዋክብት የማያፈዘው ማን አለ? “ቀዳማዊ መፍቀሬ ጥበብ”[16] ቴላስ በከዋክብት ፈዞ፣ ከገደል እንደወደቀ አንብበናል።[17] እኛስ በውበታቸው

---

[13] Philo, De Opificio Mundi, Sect. 29: “... it (the seventh day) is the festival, not of a single city or country, but of the universe, and it alone strictly deserves to be called "public" as belonging to all people and the birthday of the world.”

[14] ብጀታ፣ ድርጊት (ደስታ ተክለ ወልድ)

[15] Thomas Aquines, Compendium of Theology, Chap 68: “The first effect wrought by God in Things is existence itself, which all other effects presuppose, and on which they are based.”

[16] “ቀዳማዊ መፍቀሬ ጥበብ” ማለታችን በዲዮጅንስ The Lives and Opinions of Eminent Philosophers ኾነ በሌሎች መጽሐፍት የቅድመ ሶቅራጥስ ፈላስፎች ፊት አውራሪ በመኾኑ ነው።

[17] Plato, Theaetetus, Section, 174: “They say Thales was studying the stars... and gazing aloft, when he fell into a well; and a witty and amusing Thracian servant-girl made fun of him because, she said, he was wild to know about what was up in the sky but failed to see what was in front of him and under his feet.”

Diogenes Laërtius, The Lives and Opinions of Eminent Philosophers, Book 1, : “It is said that once, when brought outdoors by an old woman to observe the stars, he fell into a ditch, and the old woman, hearing his wail, said, “Since you can’t see what’s underfoot, Thales, do you think you’ll know what’s in the sky?”

ዓይናችን ተሰርቆ ስንቀሳቀስ እግራችን ስንቴ ተሰነካከለ? አ! አምላክ ሆይ፤ "ሥራህ ድንቅ ነው፤ ነፍሴም ይህን በውል ተረድታለች።" "የጣቶችህን ሥራ፣ ሰማያትህን ስመለከት፣ በስፍራቸው ያኖርሃቸውን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ሳይ"[18] በተደሞ ፈዘዝሁ። ውበታቸው በውነት ታላቅ ነው! ይኽን ትዕይንት ሊያደንቅ የሚችል ልሣነ ጥዑም ከየት እናምጣ? አንዳንዶች አውሬ እንዳይተናኮላቸው በዘብ ተጠብቀው ጽልመቱን በከዋክብት ላይ አፍጥጠው እንደሚያሳልፉ ሰምተናል።

ኹሉ ተፈጥሮን ያደንቃል፤ በቁሳዊና ጊዜያዊ ነገሮች አማካኝነት መንፈሳዊና ዘለዓለማዊ ምሥጢራትን ማስተዋል የሚችሉ ልበ ንጹሃን ግን ጥቂቶች ናቸው። ውበታቸው በተደሞ ፈዘን እንድንቀር ሳይኾን በእነርሱ መነሻነት ፈጣሪን እንድናውቅና እንድናመሰግን ነው። ምክንያታዊት ነፍሳችን በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ረድኤት ተደግፋ እግዚአብሔር በፍጥረቱ የገለጠውን መረዳት ትችላለች። በተፈጥሮ ውስጥ እግዚአብሔርን ለማየት ንጽሕ ሕሊና ያሻናል። ንጽሕት ሕሊና የሥነ ፍጥረትን ቋንቋ ታደምጣለች። አንገተ ደንዳና፣ ልበ ድንጋዩ ግን ዕንጨት ጠርቦ፣ ደንጊያ አለዝቦ ጣዖት በማምለክ የዘለዓለም አምላክን ክብር ምውት በኾነው ሰው፣ በወፎች፣ በእንስሳትና በምድር ላይ በሚሳቡ ፍጥረታት መልክ መስሎ ይለውጣል። ሲብስበትም ሀልዎተ እግዚአብሔርን እስከመካድ ይደርሳል። "ጠማማ ልቡና ከእግዚአብሔር ይርቃል" እንዲል።[19]

ፍጥረታት ምግበ ሥጋ፣ ምግበ ነፍስ ናቸው። "ምግበ ሥጋ መኾናቸው እሙን ነው፤ እንደ ምን ምግበ ነፍስ ተባሉ" ቢባል፦ በአፍ ሳይኾን በአእምሮ የሚላመጥ መብል በመኾናቸው ነው። እንኪያስ ወንድሜ አንባቢ ኾይ፤ ምግበ ሥጋ ለምድራዊ ሕይወት አስፈላጊ እንደኾነ ኹሉ ምግበ ነፍስ ለመንፈሳዊ ሕይወት አስፈላጊ መኾኑን ተረድተኽ ይኽን መብል ኹል ጊዜ ተመገብ!

እንዲህ ያለው ደገኛ[20] አስተምህሮ በዘመናችን ነገረ መለኮት ችል መባሉ የሚያሳዝን ነው። እኛም ይህን ተገንዝበን በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ረድኤት ታምነን፣

---

[18] መዝ 139፡14 መዝ 8፡3

[19] ጥበብ 1፡3

[20] ዋነኛ

በቀኖናዊ መጽሐፍት መሠረት፣ በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ተርጓሚነት፣ በሥነ ፍጥረት መነሻነት የመለኮትን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ለመጻፍ ጀምረናል። እግዚአብሔር በሰጠን ችሎታ መጠን እንጻፍ እንጂ ጽፈንስ ለመጨረስ ችሎታው የለንም። አንደበታችን ቢኮላተፍም የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ ከመናገር ወደ ኋላ አንልም።[21]

[21] St. Gregory, Moral 5.26: "Though our lips stammer, we yet chant the high things of God."

# መግቢያ

ቅዱሳት መጽሐፍትን እና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን በጥንቃቄ ከመረመርን በኋላ፣ ለክርስቶስ ክብር ለቤተ ክርስቲያን መታነጽ ትኾን ዘንድ ይችን ትንሽ መጽሐፍ ጻፍን። ያገኛት ኹሉ እንዲያደንቃት አንጠብቅም፤ በአስተዋዮች ዓይን የበቃች ከኾነች፣ ድኩማን ከረዳች ተሳክቶልናል።[22]

መጽሐፉን ጀምሮ ሳይጨርስ፣ ሐሳብን ከመጽሐፉ ቆንጽሎ የሚነቅፍ ቸኩል ቢገጥመን የሥነ ጽሑፍ ሕግ ከማያውቁ፣ ለአቅመ ሕያሴ ካልበቁ ሃካዮች እንደ አንዱ እንቆጥረዋለን እንጂ ስፍራ አንሰጠውም። ለምን?" ቢባል፡- ተቀዳሚውንና ተከታዩን ምንባብ ሳይመለከቱ የአንድን ክፍል ጭብጥ በምልዓት ማግኘት ስለሚያዳግት ነው። መጻፉን አንቀጽ እየለየን፣ አርእስት እየሰጠን በየፈርጁ መከፋፈላችን ኹሉ የሚፈልገውን አርእስት ቀንጭቦ እንዲያነብ አይደለም።

ደራሲው ለሰፊው የማሕበረ ሰብእ ክፍል እንግዳ ይሆናሉ ብሎ ያሰባቸውን ቃላት ፍቺ በግርጌ ማስታዎሻዎች መልክ አኑሯል። የግርጌ ማስታዎሻዎቹ ከዚህ በተጨማሪ የመጽሐፉን ጭብጥ ለመረዳት ጠቃሚ መረጃዎችን የሚያቀብሉ ናቸው። በዚህ መሠረት ተደራሲያኑ የመጽሐፉን የሐሳብ ፍሰት ተከትለው፣ የግርጌ ማስታዎሻዎቹን እያጣቀሱ እንዲያነቡ ይመክራል።

ወንድሜ አንባቢ ሆይ፤ "ጠቢብን አስተምረው፤ ይበልጥ ጥበበኛ ይኾናል። ጻድቁን ሰው አስተምረው፤ ዕውቀትን ያበዛል"[23] በተባለው መሠረት የጐደለውን መልተ፣ የጠበበውን አስፍተ እንድታነብ የፍጥረታትን ነገር ከብዙ ጥቂቱን የምትዳስስ አንስተኛ መጻፍ ጻፍኩልህ። እንግዲህ የጐደለውን መልቶ፣ የጠበበውን

---

[22] Probis probatum potius quam multis fore (the praise of honorable men is worth more than that of a multitude)

[23] ምሳ 9:9

አስፍቶ ማንበብ የአንተ የወንድሜ ድርሻ ነው። ንባብህ ምግበ ነፍስ ይኾንህ ዘንድ የድኩማን ብርታት እግዚአብሔር ዐይነ ልቡናህን ይግለጽልኽ፤ ዐይነ ነፍስህን ያብራልኽ።

# ምልከታ

የነገር መሃሉም ሆነ ፍጻሜው የቆመው ጅማሬው ላይ ነው። የነገረ ፍጥረት ጸሐፊው ወንድም ሔኖክ ነገረ ፍጻሜ በሥነ ፍጥረት ላይ መመስረቱን ሲሞግት፣ "ይኸን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጥሯልና ከመኖር ወዳለመኖር ሊያሳልፈው ሥልጣን ያለው እርሱ ብቻ በመኾኑ ነው" ይላል። ጅማሬያቸውም ፍጻሜያቸውም ፣ ጅማሬና ፍጻሜ በሌለው አስገኚአቸው እጅ ላይ እንደሆነ ይመሰክራል።

"ትውፊታዊ ማስረጃውም" ሆነ የሳይንስ ልሂቃኑ ምስክርነት በተፈጠሩት በኩል የፈጠራቸውን ለማድነቅ አገጭ ይዞ የማቃናት፣ በአክብሮት ደረት አስይዞ የማስደግደግ አቅም አላቸው። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ በደፋር ቃላት - እውነት ፈሪ ያደረገው የለምና!- ስለ ሥነ ፍጥረት አቅርቦ ፈጣሪያቸውን እንድናደንቅ ሲገፋፋን፣ ከዚህ እውነት የጎደሉትን ደግሞ "ውብና ድንቅ በኾነ ሥርዓተ ፍጥረቱ ኢ-አማናዊያንን ያሳፍራቸዋል። በሥነ ፍጥረት መካከል ያለው ድንቅ መስተጋብር አምላካዊ ጥበብ መኖሩን ያስረዳል" ሲል ይፋለማቸዋል።

ጸሐፊው ስነ ፍጥረት ብሎ ይነሳ እንጂ በአስደናቂ ሁኔታ ከልዑሉ እግዚአብሔር ማንነት ጋር ያስተዋውቀናል። ፍጥረቱን ያለፈጣሪያቸው ይዞስ የት ሊደረስ! እኛም፣ "የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያል" የሚለውን በልባችን ጽላት ላይ ጽፈን፣ "እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ" (ሮሜ 1፡20-21) እንደተባለው እንዳይሆንብን ይሄንን መጽሐፍ በማንበብ እየተባረክን እግዚአብሔርን እንድንባርክ፣ እየተደነቅን እንድናደንቅ አበረታታችኋለሁ።

በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ በዚህ መጠንና ጥልቀት የተጻፈ መጽሐፍ ያለመኖሩን ክፍተት ለመሙላት ጸሐፊው የድርሻውን በመወጣቱ ሊመሰገን ይገባል።

መልካም ንባብ!!

አበበ አብዲሳ (ጸሐፊና ተርጓሚ)

# በመዠመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ

“በመዠመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ።”[24] ግሩም ኃይለ ቃል! ሥጋዊ ደማዊ ሰው ተጠበ የፈጠረው ትርክት ሳይኾን እግዚአብሔር በባሪያው አድሮ የገለጠው እውነት። “ይኽ አምላክ የገለጠው እንጂ ሰው የፈጠረው አይደለም” እንዲል ቅዱስ አምብሮስ በሄክሳሜሮን።[25] ሊቀ ነቢያት ሙሴ ይኽ ታላቅ መለኮታዊ ግብር በተፈጸመ ጊዜ ቀርቦ የተመለከተ ይመስል ዜና ፍጥረትን ዘርዝሮ መጻፉ፣ እግዚአብሔር በርሱ አድሮ የሠራው እንጂ ከልቡ አንቅቶ የጻፈው የፈጠራ ወሬ አይደለም። “ሂድ፤ እኔ እንድትናገር አደርግሃለሁ፤ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ”[26] ሲል ወደ ፈርዖን የላከው፥ ሀብተ መንፈሱን ከእርሱ ሳያርቅ ብዙ ታላላቅ ምሥጢራትን ለቤተ እስራኤል አስተማረ። እንኪያስ ወንድሜ አንባቢ ሆይ፤ በልሳነ ሙሴ የተናገረው እግዚአብሔር እንደኾነ ተረዳ![27]

እግዚአብሔር በባሪያው አድሮ፣ “በመዠመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ” ሲል ክርክርን በሚሽር ቃሉ ሥነ ፍጥረትን በተመለከተ የማይነዋወጥ የሃይማኖት ዓምድ አቁሞልናል። ይህ ብቻ ሳይኾን ዕውቀትንና ድነትን የሚሰጡ ቅዱሳት መጽሐፍት በየገጻቸው ስለዚህ ነገር እየደጋገሙ

---

[24] ዘፍ 1፡1

[25] St. Ambrose, Hexameron, Book 1, Homily 1, Chap. 3

St. John Chrysostom, Homilies on Genesis, Homily 2.4: “It was God who sent them letters, Moses who delivered them. What do the letters say? "In the beginning God made heaven and earth."

[26] ዘጸ 4፥12

[27] St. John Chrysostom, Homilies on Genesis, Homily 2.5: “Since we therefore listen to these words not as the words of Moses but as the words of the God of all things coming to us through the tongue of Moses, so, I beg you, let us heed what is said and part company with our own reasoning.”

ይናገራሉ። እኛም የእግዚአብሔርን አብርሆት ባልተከፋፈለ ኅሊና በሙሉ ልቡና በመቀበል፣ በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ የሚነሣውን ከንቱ ሐሳብ እንቃወማለን።

"**በመዠመሪያ**" ሲል "ቁስ ጥንትና ፍጻሜ የለውም" የሚሉ ስሁታንን ይነቅፋል፤ ይቃወማል። ፍጥረተ ዓለምና ህልቀተ ዓለም መኖሩ በቅዱሳት መጽሐፍት የተገለጠ፣ በቅድስት ቤተ ክርስትያን የታመነ ነው።[28]

"**እግዚአብሔር**" ሲል "ፍጥረታት በድንገት የተገኙ፣ ሰራዒና ባለቤት የሌላቸው ናቸው" የሚሉ ስሁታንን ይነቅፋል፤ ይቃወማል። የፍጥረታት ሰራዒና ባለቤት እግዚአብሔር ነው። ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ የፈጠራቸው፣ በህልውና አጽንቶ የሚያኖራቸው እርሱ ነው። ጥንቱንስ እግዚአብሔር ማለት የዓለም ጌታ፣ ሰማይና ምድርን ፈጥሮ የሚገዛ ማለት አይደለምን?[29]

ሰው "ሠራ፣ አበጀ" ቢባል እንጂ "ፈጠረ" ሊባል አይገባም። መፍጠር ከማበጀት በዓይነትም፣ በደረጃም እጅግ በጣም የላቀ ነው።[30] ፈጣሪነት ግብሩ፣ "ፈጣሪ" ስሙ የኾነው እግዚአብሔር ብቻ ነው።[31] ቅዱሳት መጽሐፍት ለመለኮት ካልኾነ በቀር ለፍጡር ፈጣሪነት ሰጥተው አይናገሩም።

---

[28] St. Ambrose, Hexameron, Book 1, Homily 1, Chap. 3: ""In the beginning", he said… lest men be of the opinion that the world was with out a beginning."

[29] Thomas Aquines, Exposition of the Apostles' Creed, Article 1: "God means the ruler and provider of all things."

[30] Hugh of St. Victor, De Sacramentis Christianae Fidei, Part 1, Section 1: "What is created is made from nothing. For what is made from something, is indeed made, but is not created, because it is not made from nothing. Therefore, God made heaven and earth; and He not only made but created them; that is, He made them from nothing."

Thomas Aquines, Summa Contra Gentiles, Book 2: On Creation, Chap 16: "To create means nothing else than to bring something into being without any pre-existing matter."

Thomas Aquines, Summa Contra Gentiles, Book 2: On Creation, Chap 21: "Creation is an action proper to God, and that He alone can create.

[31] St. Augustine, On the Trinity, Book 3. Chap. 8-9

አንዳንዴ ቅዱሳት መጽሐፍት የፈጣሪነትን ግብር "ሥራ" በማለት ገልጠው እናገኛለን። ለምሳሌ በዜና ፍጥረት፣ ሄክሳሜሮን[32] በተፈጸሙ ጊዜ፣ "እግዚአብሔር ከሠራው ሥራ ሁሉ በሰባተኛይቱ ቀን ዐረፈ"[33] የሚል ቃል ተጽፎ እናነባለን። ኾኖም "ሠራ" ቢባል፦ በዘለዓለማዊ ፍቃዱ ዐዲስ ነገርን መፈጸሙን ለማመልከት እንጂ በእኛ ዘንድ እንደሚኾን በእርሱ ዘንድ አንዳች የሠራተኛ ዕንቅስቃሴ፣ የሥራ ድካም ኖሮስ አይደለም።[34] "ሠራ" ቢባል፦ በዘለዓለማዊ ፍቃዱ ብቻ ዐዲስ ነገርን እንደ ፈጸመ ለማመልከት እንጂ በእርሱ ዘንድ የኾነ አንዳች ለውጥ ኖሮስ አይደል። "ዐረፈ" የሚለው ቃል የፈጣሪነት ግብሩን ማቋረጡን እንጂ ድካምን አያመለክትም።[35]

ወንድሜ አንባቢ ሆይ፤ የመለኮትን አይለወጤነት ተመልከት! ሥራ ተደራጊው ላይ ለውጥ መካሄዱን ብቻ ሳይሆን አድራጊው ዘንድ ያለውንም ለውጥ ያመለክታል። መለኮት ሲሠራ ግን ያለ አንዳች ዕንቅስቃሴ፣ በፍቃዱ ብቻ ነው። "በእርሱ ዘንድ መፍቀድ መሥራት ነው" እንዲሉ።[36] ዳግመኛም በዘለዓለማዊ

---

St. Augustine, City of God, Book 21, Chap. 24: "It is blasphemy to believe or to say (even before it can be understood) that any other than God is creator of any nature, be it never so small and mortal."

Thomas Aquines, Summa Theologiae, Part 1, Q, 45

[32] ስድስቱ የመፍጠር ቀናት

[33] ዘፍ 2፡2

[34] St. Augustine, City of God, Book 12, Chap. 17: "we dare not believe that God is affected in one way when He works, in another when He rests."

[35] The Venerable Bede, On Genesis, Chap 2: "Not as if He were tired from His work, but He rested from all the work because He ceased to make a new creature, for to rest means to cease; hence in the apocalypse: They had no rest, saying, Holy, Holy, Holy, that is, they did not cease to say this."

[36] St. Basil, The Hexaemeron, Homily 1, 2: "The Maker of the Universe… needed only the impulse of His will to bring the immensities of the visible world into being."

John of Damascus, De Fide Orthodoxa, Book 2, Chap. 2: "It is by thought that He creates."

The Venerable Bede, On Genesis, Chap 1: "When it (Scripture) tells that he created heaven and earth in the very beginning of creation, by such great swiftness of work it declares that he, for whom to have willed is to have done, is omnipotent."

ፍቃዱ ዐዲስ ነገርን ይፈጽማል እንጂ ዐዲስ ነገርን የሚፈጸመው እንግዳ በኾነ ፈቃድ አይደለም። ቀድሞ ያልፈቀደውን ኋላ ላይ በመፍቀድ ሳይሆን ዘለዓለማዊ ፍቃዱ ሁሉን ይከውናል።[37] ሳይለወጥ ይለውጣል። "ዐዳዲስ ነገሮች ሀልዎታቸውን በእግዚአብሔር ፍቃድ ያገኛሉ፤ በእርሱ ዘንድ ግን ለውጥ የለም" እንዲል አለቃ ጴጥሮስ ሎምባርድ።[38]

"**ሰማያትንና ምድርን**" ሲል ሰማያትንና ምድርን፣ በውስጣቸውም ያሉትን፣ በዓይነ ሥጋ የሚታዩና የማይታዩትን ኹሉ ያመለክታል። "ኹሉ በእርሱ ተፈጥሮአል፤ ከተፈጠረው ኹሉ ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም የለም" እንዲል ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ።[39]

"**ፈጠረ**"[40] ሲል ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ እንዳስገኘ ያስረዳል። ኹሉን ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ (Ex nihilo) ፈጠረ እንጂ እንደ እደ ጥበብ

---

[37] St. Augustine, City of God, Book 12, Chap. 14: "God always has been, and that man, whom He had never made before, He willed to make in time, and this without changing His design and will."

Ibid, Chap 17: "He can begin a new work with (not a new, but) an eternal design; and what He has not made before, He does not now begin to make because He repents of His former repose… But in God the former purpose is not altered and obliterated by the subsequent and different purpose, but by one and the same eternal and unchangeable will He effected regarding the things He created, both that formerly, so long as they were not, they should not be, and that subsequently, when they began to be, they should come into existence."

Hugh of St. Victor, De Sacramentis Christianae Fidei, Part 2, Section 10: "According to His will, then, He disposed what He was to make by His will; and His will was eternal, but the work of His will was not eternal. For He always willed to make, but He did not will to make always, but to make at some time what He always willed to make at some time. Thus His will was eternal as regards His work in time, since even time itself was in the eternal will, when that should come to pass which was to be."

[38]Peter Lombard, The sentences, Book 2, distiniction 1, Chap 3

[39] ዮሐ 1፡3

[40] ዕብራይስጡ "Bara" ይለዋል። የቋንቋው ሊቃውንት- Ex nihilo- እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ- ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣትን እንደሚያመለት ያስረዳሉ። ለምሳሌ፡- Abraham Ben Ezra, Midrashim on Bereshit, Chap 1

ባለሙያ ከነበረ ቁስ (Ex praejacenti material) አላበጀም።[41] "ኹሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል"[42] የሚል የመጽሐፍን ቃል ትቶ፣ ደፍሮ፣ "እደ ጥበብ ባለሙያ ኹሉን ከነበረ ቁስ አበጀ" ብሎ የሚናገር በፍጥረተ ዓለሙ የእግዚአብሔር ድርሻ ከፊል እንደኾነ ይናገራል።[43] እኛስ እርሱ የኹሉ ህልውና እንደኾነ፣ ከርሱ በቀር አንድስ ስንኳ በራሱ ህልው ኾኖ የሚኖር እንደሌ ከቅዱሳት መጽሐፍ ተምረናል።[44] ኹሉ "በእርሱ፣ ከእርሱ፣ ለእርሱ" መባሉ ለዚህ ነው። ኹሉ በእርሱ፤ ያለ እርሱ ፈጣሪነት የተገኘ አንዳች የለምና። ኹሉ ከእርሱ፤ በመወለድ ሳይኾን በመፈጠር። ኹሉ ለእርሱ፤ ኹሉም እርሱን ስለማገልገል ተፈጥሯልና።[45]

በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?[46] እርሱ ራሱ፣ "እኔ ከሀሌ ኵሉ ነኝ" ይላል።[47] ይህን በውል የሚያውቁ ቅዱሳን መላእክት፣ "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም" ሲሉ ይመሰክራሉ።[48] በዚህ መሠረት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ኹሉን በሚችል፣ ሰማይና ምድርን በፈጠረ አምላክ ታምናለች። የእግዚአብሔር ከሀሊነት በቅዱሳት መጽሐፍት የተገለጠ፣ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የታመነ ነው። የአምላክን ከሀሊነት በሙሉ ልብ በፍፁም ነፍስ የምንቀበል ከኾነ፣

---

[41] John of Damascus, De Fide Orthodoxa, Book 2, Chap. 2: "He brought all things out of nothing into being and created them, both what is invisible and what is visible. "

[42] ቆላ 1፥16

[43] St. Basil, The Hexaemeron, Homily 2, 2: "Such is the idea that they make for themselves of the divine work. The form of the world is due to the wisdom of the supreme Artificer; matter came to the Creator from without; and thus the world results from a double origin. It has received from outside its matter and its essence, and froሰm God its form and figure. They thus come to deny that the mighty God has presided at the formation of the universe, and pretend that He has only brought a crowning contribution to a common work, that He has only contributed some small portion to the genesis of beings

[44] Thomas Aquines, Compendium of Theology, Chap 68: "Matter must be produced by God's action since… everything that exists in any way at all has God as the cause of its existence."

[45] መዝ 119፥91

[46] ዘፍ 18፥14

[47] ዘፍ 17፥1

[48] ሉቃ 1፥37

ኹሉን ካለመኾን ወደ መኾን አምጥቶ መፍጠሩ ድንቁ ምንድን ነው? በአምላካዊ ኃይሉ ለምንታመን ለእኛ ይኽም በእግዚአብሔር ዓይን ቀላል ነው። ካለመኾን ወደ መኾን አምጥቶ መፍጠር ከተሣነው ከሀሊነቱ ወዴት አለ? ከሀሊነቱ የወደደውን ማድረግ መቻሉ አይደለምን?[49] የወደደውን ማድረግ ቢሳነው "ከኃሌ ኵሉ" ባልተባለ፣ እኛም ባልታመንበት ነበር።[50]

"ምንም ነገር ካለመኾን ወደ መኾን አይመጣም" የሚሉ ኹሉ የአምላክን ከኃሊነት ይክዳሉ። እኛስ ቅዱሳት መጽሐፍትን መሠረትና ምስክር በማድረግ ሰማይና ምድርን፣ የሚታየውንና የማይታየውን ካለመኾን ወደ መኾን አምጥቶ በፈጠረ ኹሉን ቻይ አምላክ እናምናለን፤ እንታመናለን። ይህ የእምነት ቋንቋ ነው፤ "ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተፈጠሩ በእምነት እንረዳለን" እንዲል።[51]

"**ፈጠረ**" ማለቱ "Ex nihilo nihil fit- ምንም ነገር ካለመኾን ወደ መኾን አይመጣም"[52] የሚሉ ጥንታውያን ፈላስፎችን ይነቅፋል፤ ይቃወማል። በዚህ ረገድ ዘመናዊው ሳይንስ ከቅዱሳት መጽሐፍትና ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጋር ይስማማል። ኾኖም "ምንም ነገር ካለመኾን ወደ መኾን አይመጣም" የሚለውን

---

[49] Ibid, Chap. 7: "He (God) is called Almighty only because He is mighty to do all He will."

Thomas Aquines, Summa Contra Gentiles, Book 2: On Creation, Chap 22: "God's power is not limited to some particular effect, but that He is able to do absolutely all things; in other words, He is omnipotent.

[50] St. Augustine, Two Books on Genesis; Against the Manichees, Book 1, Chap.6: "we should not be like those who do not believe that Almighty God could have made something from nothing, when they observe that carpenters or any workmen cannot produce anything unless they have something out of which to make it… Almighty God did not have to be helped by anything that he had not made so that he could make what he wanted. For if something that he had not made helped him to make those things he wanted to make, he was not almighty, and that is sacrilegious to believe."

Thomas Aquines, Compendium of Theology, Chap 69: "God has no need of preexisting matter from which to fashion things."

[51] ዕብ 11፥3

[52] Aristotle, Physics, 1. 34

ብሂል የሙጥኝ ያሉ የጥንታውያን ርዝራዦች በዚህም ዘመን መኖራቸው እሙን ነው።

ሳይንስ "ኹሉ ካለመኾን ወደ መኾን የመጣ ነው" ወደሚለው ድምዳሜ ከመድረሱ ከብዙ ምዕተ ዓመታት በፊት ቤተ ክርስቲያን ኹሉ ካለመኾን ወደ መኾን እንደመጣ አምና ትኖር ነበር። አበውም በዘመናቸው "ምንም ነገር ካለመኾን ወደ መኾን አይመጣም" የሚሉ ፈላስፎችን ሲቃወሙ ቆይተዋል። ወንድሜ አንባቢ ኾይ፤ "Ex nihilo nihil fit- ምንም ነገር ካለመኾን ወደ መኾን አይመጣም" የሚለውን ብሂል ያረጀ የፈጀ እንደኾነ አስተውል!

አሁን ግን ኹሉ ካለ መኾን ወደ መኾን የመጣ መኾኑን በማመን ረገድ አረማውያንም ከእኛ ወገን ኾነዋል። "ዘመነኛው ተግዳሮት ምንድን ነው?" ብትል፡- "ኹሉ ያለ ውጫዊ መንስኤ ካለመኾን ወደ መኾን መጣ" የሚል ነው። የጥንት ኢ-አማኒያን፣ "ምንም ነገር ካለመኾን ወደ መኾን አይመጣም" ሲሉ፣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳት መጽሐፍት መሠረት ኹሉ ካለመኾን ወደ መኾን የመጣ እንደኾነ ታስተምር ነበር። ዛሬ የዘመናችን ኢ-አማኒያን፣ "ኹሉ ያለ ውጫዊ መንስኤ ካለመኾን ወደ መኾን የመጣ ነው" ሲሉ፣ ምንም ነገር **ራሱን በራሱ** ካለመኾን ወደ መኾን ሊመጣ እንደማይችል ታስተምራለች።

ቅዱስ በርናርድ ምንም ነገር ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ ራሱን ማስገኘት እንደማይችል እያስረዳ የሚከተለውን ጽፏል፡-

> "…nothing is self-originating. If it be imagined that the non-existent could give itself a beginning, or that something may be before it is, I reply that both these alternatives are contrary to reason, and it clearly follows that nothing was its own beginning."[53]

---

[53] Bernard, On Consideration, Book 5, Chap. 6

“**ፈጠረ**” ማለቱ ሥነ ፍጥረት ከፈጣሪ ባሕርይ የወጣ (Ex Deo) አለመኾኑን ይገልጣል። “He is the efficient, not the material cause” እንዲል ቅዱስ በርናርድ። ወልድ ዋሕድ[54] ከአብ ባሕርይ ተወለደ እንጂ ከሥነ ፍጥረት እንደ አንዱ ካለመኾን ወደ መኾን የመጣ አይደለም። ይህም አብን በመልክ እንዲመስለው፣ በባሕርይ እንዲተካከለው አድርጐታል። ፍጥረት ኹሉ ካለመኾን ወደ መኾን የመጣ እንጂ ከእግዚአብሔር ባሕርይ የወጣ አይደለም። ስለዚህ ሥነ ፍጥረት በባሕሪያቸው ፈጣሪን እንዳይተካከሉት እናውቃለን።[55] በዚህ መሠረት፣ “አምላክ ማነኛውም ነገር ነው፤ ማነኛውም ነገር አምላክ ነው” የሚሉ Pantheists- ኹል አምላካውያንን- ከስሁታን ይቆጠራሉ። እኒህ ለእግዚአብሔር ቅሩብነትና ርኩብነት አጽንኦት ሰጥተው፣ የእግዚአብሔርን ርሑቅነትና ምጡቅነት የዘነጉ ናቸው። ይህም ስህተት በፈጣሪና በፍጥረታት መካከል መሠረታዊ የባሕርይ ልዩነት እንዳለ እንዳይገነዘቡ አድርጓቸዋል። አንተ ግን ወንድሜ አንባቢ ሆይ፤ በፈጣሪና በሥነ ፍጥረት መካከል ርኩብነት እንዳለ ኹሉ ዘኢይትረከብ መኖሩን አስተውል።

**“በመዠመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ“** ከሚለው ኃይለ ቃል የፈጣሪና የፍጥረታት ልዩነት በግልጽ ይታያል። “ፈጣሪ ከፍጥረታት በምን ይለያል?” ቢባል፦ እርሱ በራሱ ህልው ነው፤ እነርሱ በእርሱ ህልዋን ናቸው።

---

[54] አንድያ ልጅ

[55] St. Augustine, Two Books on Genesis; Against the Manichees, Book 1, Chap. 2: “Nor did He give birth to them out of Himself so that they are what He is; rather He made them out of nothing so that they are equal neither to Him by whom they have been made nor to His Son through whom they have been made.”

St. Augustine, On the Literal Interpretation of Genesis: An Unfinished Book, Chap. 1: “Thus all of creation… as been made by God, not out of the nature of God, but out of nothing. Thus nothing of the Trinity is found in all of creation apart from the fact that the Trinity created it and it was created. Hence, we may not say or believe that the whole of creation is either consubstantial with or coeternal with God.”

Bernard, On Consideration, Book 5, Chap. 6: “God forbid that out of His own incorrupt and incorruptible substance He should be thought to have made so many things that are doubtless good, but are nevertheless corruptible.”

ለሕልውናው ውጫዊ መንስኤ የለውም። ስለዚኽ “ብሑተ[56] ሕላዌ -ብቻውን ነዋሪ” ይባላል። ነዋሪነት የእግዚአብሔር ነው። ፍጥረታት ኹሉ ካለ መኾን ወደ መኾን የመጡ ናቸው። [57] እርሱ ጥንት የሌለው ቀዳማዊ፣ ፍጻሜ የሌለው ደኃራዊ ነው። ቅድመ ዓለም የነበረ፤ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ነው። እነርሱ ጥንትና ፍጻሜ አላቸው። እርሱ በባሕርይው ጽኑ ነው፤ እነርሱ ተለዋጭ ናቸው። ፍጥረት የሚል መጠሪያቸው ሳይቀር ካለ መሆን ወደ መሆን መለወጥን የሚገልጥ አይደለምን? “መፈጠር ማለት ካለ መኾን ወደ መኾን መለወጥ ማለት ነው” እንዲል አፍላጦን። [58] እግዚአብሔር ግን ቅድመ ዓለም የነበርኩ፣ ዓለምን አሳልፌ የምኖር ነኝ ሲል “እኔ፣ ያለሁና የምኖር ነኝ” ይላል። ከዚህ በላይ ዘለዓለማዊነትን የሚገልጥ ምን አለ?

> “Do you ask, ‘What is His name?’ That is surely not a better question than ‘What is His character?’ The answer which God wished to be given respecting Himself, the answer which He Himself taught Moses, and which Moses at God’s command told the people was—**‘I am what I am**; He who is hath sent me unto you’. Fitly was this answer given. Nothing could better describe eternity, and God is eternal.” [59]

---

[56] ብሑት- የባተ፣ ብቸኛ የኾነ፣ ብቸኛ (አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ)

[57] Bernard, On Consideration, Book 5, Chap. 6: “He is self existant. He is existence for all else. And so, in a certain sense, He is alone, who is the source of His own existence, and of the existence of all beside.”

Thomas Aquines, Compendium of Theology, Chap 68: “Existence belongs to Him in virtue of His essence, but pertains to all other things by the way of Participation.”

[58] Plato, Definitions: “Genesis/Becoming: Change into being; Passing into existence.”

[59] ዘጸ 3፡14

Bernard, On Consideration, Book 5, Chap. 6

# ሥነ ሰብእ

ሥነ ሰብእ በዜና ፍጥረት ሠፊ ሽፋን የተሰጠው በመኾኑ አንቀጽ ለይተን ስለ ሰው አፈጣጠር ልንጽፍ መልካም ኾኖ ታየን። በዜና ፍጥረት ሰው፡- የሄክሳሜሮን መደምደሚያ፣ የመጨረሻው ድንቅ፣ ትንሹ ዓለም፣ አምሳለ ሥላሴ፣ መላእከ ምድር! ኾኖ ተገልጧል።

ሰውን "**የሄክሳሜሮን መደምደሚያ፣ የመጨረሻው ድንቅ**" ማለታችን፡- እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን፣ በውስጣቸውም ያሉትን ኹሉ በፈጠረ ጊዜ መጨረሻ ላይ፣ በስድስተኛ ቀን ስለፈጠረው ነው። ዜና ፍጥረት በትልቁ ዓለም መፈጠር ዠምሮ በትንሹ ዓለም መፈጠር ያበቃል።[60] "የመጨረሻው ድንቅ" ቢባል፡- መጨረሻነቱ በጊዜ ቅደም ተከተል እንጂ በክብር አይደለም።[61]

---

[60] Abraham Ben Ezra, Midrashim on Bereshit, Chap 1, Ver. 26: "He (Moses) commenced with the macrocosm and concluded with the microsm."

[61] Hugh of St. Victor, De Sacramentis Christianae Fidei, Book 1, Part 1: "The creation of man was certainly posterior in time to the creation of all visible things, but prior in cause, because all things were made for his sake who was made after all things."

Philo, De Opificio Mundi, Sect. 29: "The fact of having been the last to come into existence does not involve an inferiority corresponding to his place in the series."

ሰውን "**ትንሹ ዓለም- Microcosm**" ማለታችን፦ በባሕርያተ *ሥጋ* እና በባሕርያተ ነፍሱ ከግዑዛን እስከ መላእክት ያሉ ባሕርያትን ስለሚያሳይ ነው።።[62] በ*ሥጋ*ው ቁስነት ከግዑዛን *ጋ*ር፣ በእድገት ዘር በመተካቱ ከዕጸዋት *ጋ*ር፣ ድምጽ በማሰማት በእንቅስቃሴው ከእንስሳት *ጋ*ር፣ በምክንያታዊት ነፍሱ ከመላእክት *ጋ*ር አንድ ነው። ኾኖም እንደ ግዑዛን ያይደል በማደግ፣ በርቢ፣ በመመገብ "ሕያዋን" እንደ ሚባሉ እንስሳትና ዕጸዋት ያለ ነው፤ እንደ ዕጸዋት ያይደል እንደ እንስሳት ተንቀሳቃሽ ነው፤ እንደ እንስሳት ያይደል እንደ መላዕክት ማሰብና ማወቅ የሚችል ነው።

ሰው "Microcosm within the Macrocosm- በትልቁ ዓለም ውስጥ የሚኖር ትንሽ ዓለም"[63] ቢባል፦ ትንሽነቱ በመጠን እንጂ በክብር አይደለም። ዓለም ለሰው ልጅ ተፈጠረች እንጂ የሰው ልጅ ለዓለም አልተፈጠረም።[64] ነፍሱ

---

[62] Nemesius, On the Nature of Man, Section 1: "binds together in himself mortal and immortal elements, and joins the rational with the non-rational; who carries in his own nature the image of the whole creation, for which reason he was also called a **microcosm**."

John of Damascus, De Fide Orthodoxa, Book 1, Chap. 12: "The bond of union between man and inanimate things is the body and its composition out of the four elements: and the bond between man and plants consists, in addition to these things, of their powers of nourishment and growth and seeding, that is, generation: and finally, over and above these links man is connected with unreasoning animals by appetite, that is anger and desire, and sense and impulsive movement… Lastly, man's reason unites him to incorporeal and intelligent natures, for he applies his reason and mind and judgment to everything, and pursues after virtues, and eagerly follows after piety, which is the crown of the virtues. And so man is a **microcosm**."

[63] Ibid, Chap. 12

[64] Nemesius, On the Nature of Man, Section 1: "it was for his sake that non-rational animals and the inanimate came to be… for that reason he was also established as their ruler."

እግዚአብሔርን ስለማገልገል ተፈጥራለች። ሥጋው ነፍሱን ስለማገልገል ተፈጥሯል። ዓለም ሥጋውን ስለማገልገል ተፈጥሯል። በዚኽ ኹሉ ተጠቃሚው ሰው ነው።[65]

ሰውን "**አምሳለ ሥላሴ**" ማለታችን፦ እግዚአብሔር "ሰውን በእኛ አምሳል፣ በእኛ አርዓያ እንፍጠር" ሲል ስለፈጠረው ነው። "እንፍጠር" ማለቱ የሦስቱን አካላት የማትነጣጠል አንዲት ግብር የሚያሳይ ሲኾን፣ "በመልካችን፣ በምሳሌያችን" ማለቱ የሦስቱን አካላት አንድ መልክ፣ አንድ ባሕርይ፣ አንድ መለኮት የሚያሳይ ነው።[66] በዚህ መሠረት የክርስትና ሃይማኖት ሰው በአምሳለ ሥላሴ እንደተፈጠረ ያስተምራል። "በመልካችን፣ በምሳሌያችን" የተባለው ለመላእክት ነው" የሚሉ፣ ምሥጢረ ሥላሴን የሚክዱ ስሁታን በእኛ ዘንድ ቅቡልነት የላቸውም።[67]

እግዚአብሔር ሰውን ሊፈጥር በወደደ ጊዜ፣ ከፈጠራቸው ፍጥረታት ኹሉ አልቆና አክብሮ፣ በራሱ መልክ ፈጠረው።[68] "በእግዚአብሔር መልክ (Imago Dei)

---

[65] Hugh of St. Victor, De Sacramentis Christianae Fidei, Prologue: "The world was made for the sake of man; the soul indeed, for the sake of God; the body, for the sake of the soul; the world, for the sake of the body of man, that the soul might be subject to God, the body to the soul, and the world to the body." "God wished man to serve Him, in such a way, however, that by this service, not God, but man himself in serving should be helped, and He wished that the world serve man, and that from it man likewise should be helped, and that all good should belong to man, because for man's sake all this was made. Therefore, all good belonged to man, that is, both what was made for his own sake, and that for whose sake he himself was made. However, one good was below and was taken from below for his necessity; the other good was above, and was taken from above for his happiness."

[66] The Venerable Bede, On Genesis, Chap 1, Ver 26: "In saying let us make, the one operation of the three persons is shown; but in saying in our image and likeness, the one and equal substance."

[67] Abraham Ben Ezra, Midrashim on Bereshit, Chap 1, Ver. 26: "In the image of God means in the image of the angles."

Peter Lombard, The sentences, Book 2, distiniction 16, Chap 2: "For it said in the person of the Father to the Son and the Holy Spirit, and not, as some hold, to the angles."

[68] ዘፍ 1፡27

ተፈጠረ" ቢባል፦ በገዢነት ስለሚመስለው እንጂ በአካላዊ ቅርጽ መስሎትስ አይደለም።[69] በጌትነት ጌታውን መስሎ ሥነ ፍጥረታትን ይገዛል። ይህም ክቡር ዳዊት፣ "በእጆችህ ሥራ ላይ ሾምኸው፤ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛህለት" እንዳለው ነው።[70] ሰው ለእግዚአብሔር አገልጋይ፣ ለፍጥረታት ገዢ በመሆኑ "የፍጥረታት ዘውድ" ይባላል።[71] የእግዚአብሔር እንደራሴ ኾኖ ሥነ ፍጥረትን ይገዛል።[72]

ገዢነቱ በሰውነቱ ግዝፈት ወይም በጡንቻው ፍርጣሜ የተገኘ አይደለም። ከእርሱ በመጠን የሚገዝፉ፣ በጡንቻ የሚፈረጥሙ መኖራቸው ከክርክር ቀጠና ውጪ ያለ ሐቅ ነው። "እንኪያስ ገዢነቱን በምን አገኘው?" ቢሉ፦ በምክንያታዊነቱ! በምክንያታዊነት ከሰማይ በታች፣ ከምድር በላይ በአራቱ ማዕዘናት ተከበው የሚኖሩ ቁሳውያን ፍጥረታትን ይገዛል። የሰውነቱ ቀጥ ማለት ምክንያታዊት ለምትኾን ነፍሱና ለገዢነቱ የሚስማማ ነው።[73]

ሰውን "**መላእከ ምድር**" ማለታችን፦ እግዚአብሔር እንደ አርያማውያን መላእክት በምድር ስሙን ሊቀድስ፣ ክብሩን ሊወርስ ስለፈጠረው ነው። ዳግመኛም ድነት ሲደረግለት ከአርያማውያን መላእክት ጋር አንድ ማኅበር ኾኖ፣ በነጽሮተ እግዚአብሔር ረክቶ ተደስቶ ስለሚኖር ነው። ሰውን በግብሩ መጥራት

---

[69] Philo, De Opificio Mundi, Sect. 23: "Let no one represent the likeness as one to a bodily form; for **neither is God in human form, nor is the human body God-like**. No, it is in respect of the Mind, the sovereign element of the soul, that the word "image" is used."

[70] መዝ 8፥6

[71] Peter Lombard, The sentences, Book 2, distiniction 1, Chap 4: "Just as man was made for God, that is, to serve Him, so the world was made for man, namely to serve him. And so man was placed in the middle, so that he might serve and be served; that he might take both and all might redound to the good of man; both the obedience which he receives and that which he extends."

[72] Philo, De Opificio Mundi, Sect. 29: "… like a governor subordinate to the chief and great King."

[73] Peter Lombard, The sentences, Book 2, distiniction 16, Chap 3: " In the body, he has some property which indicates this, because his structure is erect, so that the body suits the rational soul because it is erect toward heaven."

ልሙድ ነው። እንኪያስ ለእንስሳት ተስማሚ በሚኾን ሥጋዊ ግብር ሲገኝ ከዱር እንስሳት ቢቆጠር፣ ለመላአክት ተስማሚ በሚኾን መንፈሳዊ ግብር ሲገኝ ከመላእክት ቢቆጠር ብርቱ ምንድን ነው? በባሕርይ ባይኾንም በግብር ከእነርሱ እንደ አንዱ ኾኗል።

መላእክት የምታስመስል፣ ክፋትንም በጐነትንም በራሷ ሥልጣን መፈጸም የሚቻላት፣ በሥጋ ውስጥ የምትኖር ነባቢት ነፍሱ ከግዑዛን፣ ከዕጽዋትና ከእንስሳት ብልጫ ሰጥታዋለች። በእርሷም እንደ ብርሃናውያን መላእክት ለእግዚአብሔር መታዘዝና እንደ ጽልመታውያን መላእክት በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ እንዲችል ኾኖአል። የሰማይ መላእክትን መስሎ ቢኖር ከመላእክት ጋር በአንድ ማሕበር ኾኖ በሰማያዊ መንግሥት ዘለዓለም ይኖራል።

# ርኩብ

ሠራተኛው በሥራው እንዲታወቅ ፈጣሪም በፍጥረታት መነሻነት የሚታወቅ (ርኩብ) ነው። ታይቶ የማይታወቅ እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረታት በመመርመር ይታወቃል።[74] "በግብር የሚታወቅ ባሕርይ" እንዲሉ፣ የእግዚአብሔር ባሕርይ በግብሩ ይታወቃል።

"ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራሉ… ንግግር የለም፤ ቃል የለም፤ ድምፃቸው በጆሮ የሚሰማ አይደለም። "[75] ፍጥረታትን ጆሮ ሰጥቶ ለሚሰማቸው፣ እንደ መጽሐፍ ገልጦ ለሚያነባቸው ስለ ፈጣሪ ያለ ማቋረጥ ይናገራሉ። ይናገራሉ፤ በድምጽ አይደለም። ያወራሉ፤ በቃል አይደለም። በጆሮ የሚገባ ድምጽ፣ አየር ላይ የሚፈስ ቃል የለም። እነርሱ ከንፈር ሳያንቀሳቅሱ ይናገራሉ፤ አንደበት ሳይከፍቱ የማይታየው የእግዚአብሔርን ባሕርይ ገልጠው ያሳያሉ። እኛም በጆሮ ያይደል፣ በልቡናችን እንሰማቸዋለን።

*What though in solemn silence all*
*Move round the dark terrestrial ball;*
*What though nor real voice nor sound*
*Amid their radiant orbs be found;*

*In reason's ear they all rejoice,*
*And utter forth a glorious voice,*

---

[74] ሮሜ 1፡20
[75] መዝ 19፡1-4

*For ever singing as they shine,*
*'The hand that made us is divine."*[76]

መላለሙ የፈጣሪ ምስበክ፣ የነጽሮተ እግዚአብሔር መግቢያ በር ነው። ሥነ ፍጥረት ስለ ፈጣሪ የምንማርበት ትምህርት ቤት ነው።[77] ዓይናችንን ገልጠን ፍጥረታቱን አለማየት እስካንችል ድረስ በዙሪያችን ታማኝ ምስክሮቹን አቁሟል። ፍጥረታት የፈጣሪ ታማኝ ምስክሮች ናቸው።[78] የሚታየው ፍጥረት የማይታየውን ፈጣሪ ያሣያል። ሥነ ፍጥረት የነገረ መለኮት መምህር ነው። ወንድሜ አንባቢ ኾይ፤ ሃልዎተ እግዚአብሔር የሚክዱ፣ ባሕርየ እግዚአብሔር በፍጥረታት መስለው የሚለውጡ ማመካኛ እንደሌላቸው በዚህ ተረዳ![79]

ሰው በአእምሮ ተመራምሮ ፈጣሪውን ሊያውቅና ስሙን ሊቀድስ፣ ክብሩን ሊያወድስ ተፈጥሮአል። "የሰውን ዘር ኹሉ ከአንድ ወገን ፈጥሮ በምድር ኹሉ ላይ እንዲኖሩ አደረገ፤ የዘመናቸውን ልክና የመኖሪያ ስፍራቸውንም ዳርቻ ወሰነላቸው። ይኸውም ሰዎች እግዚአብሔርን ፈልገው ተመራምረው ምናልባት ያገኙት እንደኾነ ብሎ ነው" እንዲል ቅዱስ ጳውሎስ ለአቴና ሰዎች።[80] ኾኖም በአእምሮ ተመራምሮ ፈጣሪውን ሊያውቅና ስሙን ሊቀድስ ክብሩን ሊያወድስ ተፈጥሮ የነበረ ሰው፣ አንዱ **ሀልዎተ እግዚአብሔርን**[81] እስኪክድ ድረስ በንዋመ[82] ሐኬት ሰጠመ። ሌላው "**ባሕርየ እግዚአብሔርን** በጣዖታት ለወጠ።[83]

---

[76] Joseph addison, The spacious firmament on high

[77] St. Basil, The Hexaemeron, Homily 1, 6: "It (creation) is really the school where reasonable souls exercise themselves, the training ground where they learn to know God; since by the sight of visible and sensible things the mind is led, as by a hand, to the contemplation of invisible things.

[78] መዝ 89፡37

[79] ሮሜ 1፡ 20

[80] ሐዋ 17፡26-27

[81] የእግዚአብሔር መኖር

[82] ንዋም- እንቅልፍ፣ ሽልብታ፣ መኝታ፣ ሞት፣ ፍጹም ዕረፍት (አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ)

[83] ሮሜ 1፡23

# ሀልዎተ እግዚአብሔር

ፈጣሪ ለፍጥረቱ በፍጥረቱ በግልጽ ይታያል። አንዳንዶች በፍጥረታት መነሻነት የመለኮትን ነገር መማር ቢሳናቸው መዝሙረኛው እንዳለው፣ "ለእግዚአብሔር ሥራ ግድ ስለሌላቸው፣ ለእጆቹም ተግባራት ስፍራ ስላልሰጡ" ነው።[84] ልበ ደንጊያ፣ አንገተ ደንዳና በመኾናቸው በሥራው ውስጥ ሠሪውን እንዳይመለከቱ ታውረዋል።

ስለዚህ ልቡናቸው ተሞኘ፤ አእምሯቸው ደነዘዘ ። "እግዚአብሔር ሆይ፤ ሥራህ እንዴት ታላቅ ነው!... ደነዝ ሰው ይህን አያውቅም፤ ሞኝም አያስተውለውም" እንዲል ክቡር ዳዊት።[85] እኒህ አምላካዊ ኃይል መኖሩን የሚክዱ "ኢ-አማኒያን" ይባላሉ። እነርሱ ፍጥረታት ስለ ፈጣሪ ሚሉትን የሚሰሙበት ጆሮ፣ የሚያስተውሉበት ልቡና ስላጡ የእጁን ሥራ እያዩ ሠሪውን ይክዳሉ።

ንፋስ በባሕርዩ ረቂቅ ከመኾኑ የተነሳ በዓይን ሊታይ አይችልም። ነገር ግን በዓይን ማየት ስላልቻልን ብቻ የለም ማለት አይደለም፤ መኖሩ በሥራው በግልጽ ይታወቃልና። እንዲኹም የማይታየው እግዚአብሔር በሥራው በግልጽ ይታወቃል። ነፍስ በሰው ውስጥ እንደማትታይ ግን በሰውነት እንቅስቃሴ እንደምትታወቅ፣ እግዚአብሔርም በሥጋዊ ዐይን አይታይም፤ ግን በሥራው ይገለጣል። አንተ፣ "ሲፈጥር ማን አየው?" ትላለህ፤ ሲፈጥር ባናየውም፣ የፈጠረውን አይተናል። ለሥዕል ሠዓሊ እንዳለው ሁሉ ለፍጥረት ፈጣሪ አለው።

---

[84] መዝ 27 (28)፡5

[85] መዝ 92፡5-6

ውብና ድንቅ በኾነ ሥርዓተ ፍጥረቱ ኢ-አማናውያንን ያሳፍራቸዋል። በሥነ ፍጥረት መካከል ያለው ድንቅ መስተጋብር አምላካዊ ጥበብ መኖሩን ያስረዳል። ፈጣሪ ፍጥረትን በፍጥረት ይመግባል፤ ከእነርሱ የአንዱ ህልውና በሌላው ላይ  የሚደገፍ ነው።[86] የሥነ ፍጥረት ድንቅ መስተጋብር ለአእምሯችን ከቀረቡ የሀልዎተ እግዚአብሔር ማስረጃዎች አንዱ ነው። ይኽን በአስተውሎት የመረመረ ሥነ ፍጥረት በመለኮታዊ ጥበብ እንደተበጀ ይገነዘባል።[87]

እንኪያስ ፍጥረታት እርስ በእርሳቸው ተደጋጋፊ ከኾኑ፣ እንዴት አብልጠው በፈጣሪያቸው ላይ አይደገፉ? ፍጥረታትን ከአከባቢያቸው ጋር አስማምቶ የፈጠረ፣ ከራሱ ጋር እንዲራከቡ አድርጎ በመፍጠሩ ከስርዓተ ምህዳር ጋር ብቻ ሳይኾን ከፈጣሪም ጋር ግሩም መስተጋብር አላቸው። በተለይ በልቦናው Sensus Divinitatis- የመለኮት ህልውና እንዲሰማው፣ በአእምሮው ተመራምሮ እግዚአብሔርን እንዲያገኝ የተፈጠረ ምክንያታዊው ሰው ይህን ይረዳል።[88]

መልካም የሚሠራ ዋጋ እንደሚያገኝ፣ ክፉ የሚሠራ እንደሚቀጣ ሕሊናው ይመሰክርበታል። ይህ በራሱ ለኹሉ እንደ ሥራው የሚሰጥ አንድ ገዢ መኖሩን የሚያረጋግጥ ነው። ገዢ ከሌለ መልካም ለሠራው ዋጋ የሚሰጥ፣ ክፉ የሠራውን የሚቀጣ ማን ነው? ቢፈጽሟት ደስ የምትሰኝ፣ ባይፈጽሟት የምትወቅስ ልቡናይት ሕግ ራሷ ሕግ ሰጪ መኖሩን የምታሳውቅ ናት።

---

[86] Thomas Aquines, Exposition of the Apostles’ Creed, Article 1: “We see how the sun, the moon, and the stars, and all natural things follow a determined course, which would be impossible if they were merely products of chance. Hence, as is spoken of in the Psalm, he is indeed foolish who does not believe in God: “The fool said in his heart: There is no God” [Ps 13:1].”

[87] John of Damascus, De Fide Orthodoxa, Book 1, Chap. 3: “The very continuity of the creation, and its preservation and government, teach us that there does exist a Deity, who supports and maintains and preserves and ever provides for this universe.”

[88] Ibid, Chap. 1: “The knowledge of God’s existence has been implanted by Him in all by nature.”

Ibid, Chap 3: “the knowledge of the existence of God is implanted in us by nature. But since the wickedness of the Evil One has prevailed so mightily against man’s nature as even to drive some into denying the existence of God.”

በገጸ ምድር የሚርመሰመሱ ሕዝቦችን አንድ ከሚያደርጉ ሰብዓዊ ባሕርያት መካከል አንዱ የአምልኮት ጠባይ እንደኾነ የሥነ ሰብእ ምሁራን[89] ይመሰክራሉ። እርሱን ለማገልገል የተፈጠሩ ዕንጨትንና ድንጋይን እየጠረበ እስኪያመልክ፣ በባሕርይ ከእርሱ ያነሱ ፍጥረታትን ጎንበስ ቀና እያለ እስኪያገለግል ድረስ ሕሊናው ምን እርግጠኛ አደረጋት? እግዚአብሔር ባይኖር ሰው ይህን የአምልኮት ጠባይ ከየት ሊያገኝ ይችላል?

የፈጣሪን ህልውና የምንክድ ከኾነ ሕይወት ትርጉም እንዳላት ለመካድ እንገደዳለን። ከንቱነት[90] ለኢ-አማኒነት ተመጋጋቢው ርዕዮተ ዓለም ነው። ፈጣሪ ከሌለ ሕልውናችን ምክንያት የለውም። ሕልውናችን ምክንያት ከሌለው ሕይወታችን ትርጉም የለሽ ናት። ሕይወታችን በተፈጠርንበት ምክንያት ይተረጎማልና። ሕይወታችን ትርጉም የለሽ ከኾነች እያንዳንዷን ቀን ወደብ እንደሌላት መርከብ፣ ጎጆ እንዳጣች ወፍ በከንቱነት እንቅበዘበዛለን።

[89] Anthropologists
[90] Nihilism

# ባሕርየ እግዚአብሔር

ፍጥረታት ሀልዎተ እግዚአብሔርን ብቻ ሳይኾን ባሕርየ እግዚአብሔርን ገልጠው ያሳያሉ። "የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ ከፍጥረቱ በግልጽ ይታያል" እንዲል ሊቀ ሐዋርያት፣ ቅዱስ ጳውሎስ። ኹሉን በመልካምነት ፈቀደ፤ በሃይል ከወነ፤ በጥበብ አስዋበ።[91] ዐይነ ልቡናቸው ለተከፈተ፣ ዐይነ ነፍሳቸው ለበራ የእግዚአብሔር መልካምነት፣ ጥበብና ሃይል ከፍጥረቱ በጉልህ የሚታይ ነው።

**መልካምነቱ** ፍጥረታትን ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ በመፍጠሩ ተገልጧል። መዝሙረኛው "ሰማያትን በብልኅት የሠራ፤ ፍቅሩ ዘለዓለማዊ ነውና። ምድርን በውሃ ላይ የዘረጋ፤ መልካምነቱ ዘለዓለማዊ ነውና"[92] ሲል የፈጣሪነት ግብሩ መነሻ መልካምነቱ እንደኾነ ይገልጣል።

ኹሉን በመልካም ፍቃዱ ፈጠረ እንጂ እንዲፈጥር የሚያስገድደው ውስጣዊ ጉድለት ወይም ውጫዊ ኃይል የለም።[93] መለኮት በራሱ ለራሱ ብቁ ነው፤ ህልውናው በፍጥረታት ላይ የተደገፈ አይደለም። ከሥነ ፍጥረት አንዳች ስንኳ "እጠቀም" ብሎ ወይም ተገዶ የፈጠረው የለም። ግዳጁን ለመወጣት፣ ጉድለቱን ለመሙላት የፈጠረው አይደለም። በፍጹም! ማን ያስገድደዋል? ምንስ

---

[91] Hugh of St. Victor, De Sacramentis Christianae Fidei, Part 2, 10: "He willed by goodness, He disposed by wisdom, He made by power."

[92] መዝ 136፡5-6

[93] Thomas Aquines, Compendium of Theology, Chap 96: "God has brought things into existence not through any necessity of His nature but by His will... God evidently produces things by His will, and not under the impulse of natural necessity."

John of Damascus, De Fide Orthodoxa, Book 2, Chap. 2: "His exceeding goodness wished certain things to come into existence which would enjoy His benefits and share in His goodness."

ይጐድለዋል? "የሚጐድለው ነገር ባለመኖሩ በሰው እጅ አይገለገልም" እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ።[94]

"እንኪያስ ለምን ፈጠራቸው?" ቢባል፦ የራሱን ክብር በእነርሱ ውስጥ፣ በእነርሱ ላይ፣ በእነርሱ በኩል ይገልጥ ዘንድ።[95] ቅዱስ በናቬንቸር እንዳለው እግዚአብሔር ኹሉን ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ ሲፈጥር፣ "ክብሩን ይገልጥና ሊያካፍል እንጂ ሊያበዛ አይደለም"።[96] ምን ጐድሎት ያበዛል? ምንስ አንሶት ይጨምራል? እርሱ እንደኾን በራሱ ለራሱ ሙሉዕ ነው። "ክብሩን አካፍሎ ፈጠራቸው" ቢባል፦ ከእርሱ የሚጐድል አንዳች ነገር እንዳለ ልናስብ አይገባም።[97]

ሥነ ፍጥረትን "እጠቀም" ብሎ ሳይኾን ክብሩን ለማካፈል በመፍጠሩ መልካምነቱ ተገልጧል።[98] "የፈጣሪን መልካምነት በምን እናውቃለን?" ቢሉ፦ በራሱ ለራሱ የበቃ ኾኖ ሳለ እኛን በመፍጠሩ። "የፍቅር ቁልፍ እጁን ስትከፍት ፍጥረታት ወደ መኾን መጡ" እንዳለ አኲይነስ።

**ጥበቡ** በሥነ ፍጥረት ውበትና መስተጋብር ተገልጧል። የፍጥረታቱን ሥነ ሥርዓት ስንመለከት የፈጣሪን ፍጹም ጥበብ እንረዳለን። መላለሙ ጥበበ መለኮት

---

[94] ሐዋ 17፡25

[95] Catechism of the Catholic Church, Part 1, sect. 1, Chap. 1: "All creatures bear a certain resemblance to God, most especially man, created in the image and likeness of God. the manifold perfections of creatures - their truth, their goodness, their beauty all reflect the infinite perfection of God. Consequently we can name God by taking his creatures perfections as our starting point, 'for from the greatness and beauty of created things comes a corresponding perception of their Creator'"

[96] St. Bonaventure, Com. On The Sentences, Book 2, Chap. 1

[97] Peter Lombard, The sentences, Book 2, distiniction 1, Chap 3: "So great is His goodness that He, as the Supreme Good, wanted others to sharers in His blessedness, by which He is eternally blessed; He saw that this could be shared and suffer no diminution at all."

[98] St. Augustine, City of God, Book 12, Chap. 17: "He would show… how independent He is of what He makes, and how it is of His own gratuitous goodness He creates, since from eternity He dwelt without creatures in no less perfect a blessedness."

የሚታይበት አዳራሽ ነው። ሥነ ፍጥረትን አተኩሮ ማየት የቻለ፣ ከመዝሙረኛው ጋር፣ “ጌታችን ታላቅ ነው፤ እጅግ ኃያልም ነው፤ ለጥበቡም ወሰን የለውም“፣ “ሁሉን በጥበብ አደረግህ“ እያለ ይዘምራል።[99]

**ከኃሊነቱ** ሥነ ፍጥረትን ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ በመፍጠሩ ተገልጧል። ሁሉን ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ የፈጠረ እርሱ ምን ይሳነዋል? አስተዋይ የሥነ ፍጥረት ታላቅነት ተመልክቶ የፈጣሪን ኃይል ያደንቃል። ወንድሜ አንባቢ ኾይ፤ ኃይል የእግዚአብሔር መኾኑን ከፍጥረቱ ተረዳ! ክቡር ዳዊት በመዝሙሩ፣ ”በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ተሠሩ፤ በአፉም እስትንፋስ የከዋክብት ሰራዊት” ካለ በኋላ፣ ”ምድር ኹሉ ትፍራው፤ በዓለም የሚኖር ሕዝብ ሁሉ በፊቱ ይንቀጥቀጥ” ሲል ፈጣሪ የሚያርድ የሚያንቀጠቅጥ ታላቅነት ባለቤት መኾኑን በሥነ ፍጥረት መነሻነት ይናገራል።[100]

የእግዚአብሔር ባሕርይ ከፍጥረቱ በግልጽ የሚታይ ቢኾንም አንዳንዶች የእግዚአብሔርን ባሕርይ በመዋቲ ሰው፣ በወፎች፣ በእንስሳትና በምድር ላይ በሚሳቡ ፍጥረታት አምሳል ተኩ። እግዚአብሔርን ሲያውቁት ካዱት እንጂ እንደ እግዚአብሔርነቱ አላከበሩትም፤ ዕንጨት ጠርበው፣ ደንጊያ አለዝበው አመለኩ። ፈጣሪን ትተው በግብረ እደ ሰብእ[101] ታመኑ። ”ሠሪው በገዛ እጁ ሥራ ይታመናል” እንዲል።[102]

የእግዚአብሔር መልካምነት ከፍጥረቱ በግልት ይታያል፡፡ ኾኖም የእርሱና የእነርሱ መልካምነት ለየቅል ነው።[103] ሠናይነት በእርሱ ዘንድ የባሕርይ፣ በእነርሱ

---

[99] መዝ 147፡5 መዝ 104፡24

[100] መዝ 33፡6-8

[101] በሰው እጅ ሥራ

[102] ዕም 2፡18

[103] St. Augustine, Two Books on Genesis; Against the Manichees, Book 1, Chap.2: “All the things that God has made are very good, but they are not good in the same way that God is good.”

ዘንድ የሱታፌ ነው።[104] እርሱ በራሱ ሠናይ፣ እነርሱ በእርሱ ሠናያን ናቸው። እርሱ ከሠናያን አንዱ ሳይኾን ሠናያን ሁሉ የሠነዩበት ምሥናይ ነው።[105] ነፍሳችንን የሚያረካ ሥያኔ[106] በፍጥረታት ዘንድ በሱታፌ ያለ ሥያኔ ሳይኾን በፈጣሪ ዘንድ የባሕርይ የኾነ ሥያኔ ነው።

"እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም፣ እጅግ መልካም ነበረ" የሚለውን ቃል ትቶ፣ ደፍሮ ከሥነ ፍጥረት አንዳንዱን "እኩይ" እያለ የሚያክፋፋ ቢኖር በእኛ ዘንድ ከስሁት ይቆጠራል፡፡ እግዚአብሔር መልካምና ጠቢብ በመኾኑ እኩይና ያልበቃ ነገር አልፈጠረም። [107] ከእጆቹ ሥራዎች መካከል አንዳች ስንኳ እኩይ የለም። ቅዱሳት መጽሐፍት ክርክርን በሚሽር ቃል፣ "እግዚአብሔር ኹሉን እጅግ ሠናይ፣ ውብም አድርጎ ሠራ"[108] በማለት የእግዚአብሔርን እጅ ሥራ ያደንቃሉ።

ኾኖም ጠርጣራ አእምሮአቸው፣ "ይህ ለምን ኾነ?" "ያ ለምን ኾነ?" እያለ በሥነ ፍጥረት ውስጥ ሕጸጽ ፍለጋ ይንከራተታል እንጂ በቃለ እግዚአብሔር ረክቶ አይቀመጥም። "ዓለም በረብ የለሽና ጐጂ ፍጥረታት ተሞልታ ሳለ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት "ኹሉ መልካም፣ ያማረ ነው" ይላል?" ቢሉ፦ እነርሱ ማስተዋል ተሳናቸው እንጂ በእግዚአብሔር ዕይታ ኹሉ ውብና ድንቅ ነው።

*"God does not judge of the beauty of His work by the charm of the eyes, and He does not*

---

[104] Thomas Aquines, Summa Theologiae, Part 1, Q, 6: "Boethius says (De Hebdom.), that "all things but God are good by participation." Therefore they are not good essentially... it is manifest that God alone has every kind of perfection by His own essence; therefore He Himself alone is good essentially."

[105] ሠናይ (ይት:ያን:ያት)- መልካም፣ ውብ፣ ደግ
ምሥናይ- ማማረያ፣ መዋቢያ (አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ)

[106] ሠናይነት

[107] St. Augustine, On the Trinity, Book 8, Chap. 3: "This thing is good and that good, but take away this and that, and regard good itself if thou canst; so wilt thou see God, not good by a good that is other than Himself, but the good of all good."

[108] ዘፍ 1፡31 መክ 3፡11

*form the same idea of beauty that we do. What He esteems beautiful is that which presents in its perfection all the fitness of art, and that which tends to the usefulness of its end."* [109]

ሙያ የሌለው ሰው በባለ ሙያ ሆርሻ[110] ውስጥ ቢገኝ ብዙ መሳሪያዎችን ይመለከታል፤ ኾኖም የአንዳንዱን ጥቅም ላይረዳ ይችላል። እኛም ሥነ ፍጥረትን ስናስብ፣ የአንዳንዱ ጥቅም ባይገባንም በእግዚአብሔር እጅ ጠቃሚ መሳሪያዎች እንደኾኑ ልንረዳ ይገባል። አንዳች ስንኳ ያለምክንያት የተፈጠረ ነገር የለም።

ፍጥረታት ኹሉ መልካም መኾናቸውን ስንሰማ ጥቅም አልባ እና ጐጂ ነገሮችን በማሰብ፣ "እኒህስ እንዴት መልካም ሊኾኑ ይችላሉ?" የሚል ጥያቄ ይፈጠርብናል። ጐጂ በሚል ጐራ የምንመድባቸው ነገሮች እግዚአብሔርን በአሉታዊ መንገድ ያገለግሉታል። እኒህ እግዚአብሔር ለአንዳንዶች ተግሣጽን፣ ለሌሎች ቅጣትን የሚሰጥበት በትር ናቸውና። ጥቅም አልባ ስለኾኑ ነገሮች መጠየቅ ምን ያደርግልናል? ስላልጠቀሙን ደስባይለን እንኳ ስላልጐዱን ደስ ይበለን። ለቤታችን፣ ለግል ፍጆታችን ባያስፈልጉም በስርአተ ምህዳራቸው ውስጥ ባላቸው ተመጋጋቢነት አስፈላጊ ናቸው። ስለዚህ የሚጠቅመውን ተጠቀም፣ ጐጂን ተጠንቀቅ፣ የማይጠቅምህን ተወው።[111]

ኃጢአት ወደ ምድር ከመግባቱ በፊት ቅጣትና ፍርድ ባለመኖሩ፣ ቅድመ ውድቀት ጐጂ ነገሮች በምድር ላይ ምን ፈይዳ ነበራቸው? ቢባል፦ በጐጂ መደብ ከምንመድባቸው አንዳንዶቹ ከውድቀት በኋላ ምድር ያስገኘቻቸው ናቸው።[112]

[109] St. Basil, The Hexaemeron, Homily 3, 10

[110] የሥራ ስፍራ

[111] St. Augustine, Two Books on Genesis; Against the Manichees, Book 1, Chap.16

[112] Ibid, "The earth was cursed by reason of the sin of man so that it bears thorns, not that it should suffer punishment since it is without sensation, but that it should always set before the eyes of men the judgment upon human sin. Thus

ሌሎቹ ከውድቀት በፊት ቢኖሩም ከአዳም እግር በታች ተገዝተው፣ ጉዳት አልባ ነበሩ።[113] አዳም ጌታው ላይ ባመጸ ጊዜ ግን እነርሱም አዳም ላይ አመጹ እንጂ በጥንተ ተፈጥሯቸውስ እንዲህ አልነበረም። ከሥነ ፍጥረት ማናቸውንም ነገር "እኩይ ነው" ብለን ልንነቅፍ አይገባም።

men might be admonished by it to turn away from sins and to turn to God's commandments."

Peter Lombard, The sentences, Book 2, distiniction 15, Chap 4: "It may be said that those which are born from bodies of animals, particulary of deed ones, were not created with the animals, except potentially and materially."

[113] Ibid, Chap 3: "It can unequivocally be said that created things would have done no harm to man, If he had not sinned, for they began to be harmful in order to punish vices and scare their practitioners, or to test and perfect virtue. And so they were created harmless, but were made harmful because of sin."

# መግቦተ እግዚአብሔር

"ፈጣሪ ሥነ ፍጥረትን ካስገኘ በኋላ ከሥነ ፍጥረት ተለይቶ ብቻውን ይኖራል፤ የገሃዱ ዓለም እንቅስቃሴ ከእግዚአብሔር ጥበቃና ቁጥጥር ውጭ ነው" የሚሉ ሥነ ፍጥረትን ያለ መጋቢ ያስቀራሉ። በእኛ ዘንድ ሃይማኖት እግዚአብሔርን በፈጣሪነቱ በመቀበል የምታበቃ ሳትኾን መጋቢነቱና አዳኝነቱንም በመታመን የምትቀጥል ናት። እግዚአብሔር ኹሉን ካለ መኾን ወደ መኾን አምጥቶ ከፈጠረ በኋላ ኹሉን በመግቦቱ ደግፎ ይዞአል እንጂ ከፍጥረቱ አልተለየም።[114] "መግቦት" የምንለው እግዚአብሔር ለሥነ ፍጥረት የሚወስደው ጥንቃቄ ነው።[115] ወልዶ እንደሚንከባከብ አባት፣ ፈጥሮ ይመግባል።

በሰባተኛው ቀን "እግዚአብሔር ከሥራው ዐረፈ"[116] የሚል ተጽፎ ብታገኝ፣ የፈጣሪነት ግብሩን በማቋረጡ እንጂ በመግቦተ ዓለሙ እስከ ዛሬ ይሠራል።[117] ይኽ በቅዱሳት መጽሐፍት የተገለጠ፣ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የታመነ ነው። ፈጣሪ ቃል ሥጋ ኾኖ፣ "አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል፤ እኔም ደግሞ እሠራለሁ" ያለውን ቃል ትተው፣ "እግዚአብሔር ከሥነ ፍጥረት ጋር ያለውን ግንኙነት በሄክሳሜሮን ቋጭቷል" የሚሉ በእኛ ዘንድ ውጉዛን ናቸው።[118]

---

[114] Nemesius, On the Nature of Man, Section 42: "To creation belongs the making well of things that come to be, to providence the good care of things that come to be."

[115] Nemesius, On the Nature of Man, Section 42
John of Damascus, De Fide Orthodoxa, Book 2, Chap. 29

[116] ዘፍ 2፡2

[117] St. Augustine, On the Literal Interpretation of Genesis, Book 4, Chap 3: "… Yet even to this very day… the Father works with the Son, namely in governing all those kinds which were then established at that time."

[118] ዮሐ 5፡17

ገዢነትን ለከዋክብት ሰጥተው፣ “እጣ ፈንታችን በከዋክብት እንቅስቃሴ ይወሰናል” የሚሉ በእኛ ዘንድ ቅቡልነት የላቸውም። እንዲህ ያለው ልምምድ ከክርስትና ሃይማኖት ጋር ተፃራሪ ነው። ቅዱሳት መጽሐፍት ዕንጨት ጠርበው፣ ደንጊያ አለዝበው የሚያመልኩ ጣዖት አምላኪያንን እንደሚነቅፉ ኹሉ ሕይወታቸውን ለፍካሬ ከዋክብት የሚያስገዙትን ይነቅፋሉ።

> “የአሕዛብን መንገድ አትከተሉ፤ እነርሱ በሰማይ ምልክቶች ይታወካሉ፤ እናንተ ግን በእነዚህ አትረበሹ የአሕዛብ ልማድ ከንቱ ነውና፤ ዛፍ ከጫካ ይቈርጣሉ፤ አናጺም በመሣሪያው ቅርጽ ያበጅለታል፤ በብርና በወርቅ ይለብጡታል፤ እንዳይወድቅም፣ በመዶሻ መትተው በምስማር ያጣብቁታል። ጣዖቶቻቸው በዱባ ዕርሻ መካከል እንደ ቆመ ማስፈራርኞ ናቸው፤ የመናገር ችሎታ የላቸውም፤ መራመድም ስለማይችሉ፣ ተሸካሚ ያስፈልጋቸዋል፤ ጒዳት ማድረስም ሆነ፣ መልካምን ነገር ማድረግ ስለማይችሉ፣ አትፍሯቸው።”[119]

የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት ስንመረምር ሊቃውንቱ የአስትሮሎጂን ከንቱነት እያሳዩ ያቀረቡአቸውን ብዙ ሙግት ነጥቦች እናገኛለን።[120] ለአብነት ያኽል በማሕደረ ትውስታዬ በጉልህ የታዩኝን መዘርዘር እጀምራለሁ።

እንደ አስትሮሎጂስቶቹ አስተምህሮ ደጋግ እና ጨካኝ ከዋክብት አሉ። ዳግመኛም በአንድ ኮከብ ሥር የተወለዱ ምግባራቸውና እጣ ፈንታቸው ተመሳሳይ ይኾናል። ስለዚህ ልጅ ለመውለድ ፈልገው ግብረ ሩካቤ ሲፈጽሙ ልጃቸው ታላቅ እንዲኾን የሚፀነስበትንና የሚወለድበትን ኮከብ መርጠው ነው። ትዳራቸው የሰመረ እንዲኾን ኮከብ ቆጥረው የሰርጋቸውን ቀን ይወስናሉ። ይኽ ብቻ ሳይኾን አዝዕርት ሲዘሩ አትክልት ሲተክሉ እንኳ ኮከብ ቆጥረው ነው።

---

[119] ኤር 10፡2-6

[120] ለምሳሌ፡- ይሁዲው ፊሎ የከለዳውያንን አስትሮሎጂ ተቃውሞ ጽፏል። ቅዱስ ባሲልዮስ በሄክሳሜሮን፣ ቅዱስ ኦገስጢኖስ "የእግዚአብሔር ከተማ" በተሰኘው መጽሐፉ አስትሮሎጂን ነቅፈው ጽፏል።

ወንድሜ አንባቢ ኾይ፤ ዔሳውንና ያዕቆብን ተመልከት! በአንድ ግብረ ሩካቤ ተፀንሰው፣ በተከታታይ የተወለዱ መንታዎች ናቸው። ኾኖም ምግባራቸውም ኾነ እድል ፈንታቸው እጅግ የተለያየ ነው። በአንድ ግብረ ሩካቤ ተፀንሰው፣ በተከታታይ የተወለዱ መንታዎች ምግባራቸውም ኾነ እጣ ፈንታቸው ካልተገናኘ፣ "በአንድ ኮከብ የተወለዱ ሰዎች ምግባራቸውና በእድል ፈንታቸው ተመሳሳይ ይኾናል" ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው።

የተወለድበት ኮከብ እጣ ፈንታህን የሚወስነው ከኾነ ኮከብ ቆጥሮ ቀን መርጦ የሰርግህን ቀን መወሰኑ ምን ዋጋ አለው? ከዋክብቱ አስቀድመው በልደትህ የወሰኑልህን እጦ ፈንታ የከዋክብትን ምሥጢር መርምረህ የሰርግህን ቀን በጥንቃቄ በመምረጥህ የምትሽረው ይመስልሃል? አንተ ኮከብህን ትመርጣለህ ወይስ ኮከብህ እጣ ፈንታህን ይወስናል? እባክኽ ማን የበላይ እንደኾነ ንገረኝ?

ዘሪው ዘርን ሲዘራ *"አንዳንዱ መንገድ ዳር ወደቀ፤ ወፎችም መጥተው ለቅመው በሉት። አንዳንዱ ዘር ዐፈሩ ስስ በሆነ፣ ድንጋያማ መሬት ላይ ወደቀ፤ ዐፈሩ ስስ ስለ ሆነም ፈጥኖ በቀለ። ነገር ግን ፀሓይ ሲመታው ጠወለገ፤ ሥር ባለ መስደዱም ደረቀ። አንዳንዱም ዘር በእሾኽ መካከል ወደቀ፤ እሾኹም አደገና ቡቃያውን አንቆ አስቀረው። ሌላው ዘር ደግሞ በጥሩ መሬት ላይ ወደቀ፤ ፍሬም አፈራ፤ አንዱ መቶ፣ አንዱ ሥልሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ።"*

ወንድሜ አንባቢ ኾይ፤ ዘሪው አንድ ላይ የዘራው ዘር የተለያየ ፍጻሜ ካገኘ ከኮከቡ ይልቅ የመሬቱ ዓይነት ዋጋ እንዳለው ተረዳ! ከካከብ ይልቅ መሬትና የአየር ንብረት አይቶ የሚዘራ ብልኽ ነው።

*የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ነበረ፤ "የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም ነበረ፤ የሮብዓም ልጅ አቢያ፣ የአቢያ ልጅ አሳ፣ የአሳ ልጅ ኢዮሣፍጥ፣የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም፣ የኢዮራም ልጅ*

*አካዝያስ፣ የአካዝያስ ልጅ ኢዮአስ፣የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ፣ የአሜስያስ ልጅ ዓዛርያስ፣ የዓዛርያስ ልጅ ኢዮአታም" ነበረ።*[121]

እኒ ኹሉ በመተካካት ቤተ እስራኤል ላይ የነገሱ አይደሉምን? የንጉስ ልጅ የአባቱን መንበር ወርሶ ንጉስ ሲኾን፣ የባሪያ ልጅ የአባቱ እጣ ፈንታ ተከትሎት ባሪያ ሲኾን ከዋክብቱ ከወዴት አሉ?

[121] 1ዜና 3፡ 10-12

# የእኩይ ጣጣ

እግዚአብሔር በሕጸጽ አልባ ጥበቡ፣ በመልካም ፍቃዱ፣ በከሃሌ ኩሉ ኃይሉ ባበጃጀው ዓለም ውስጥ እኩይ እንዴት ተከሰተ? ኤፊቆሮስ ይኽን ጥያቄ እንደሚከተለው አቅርቦታል፡-

> *"Is God willing to prevent evil, but not able? Then he is not omnipotent. Is he able, but not willing? Then he is malevolent. Is he both able and willing? Then whence cometh evil? Is he neither able nor willing? Then why call him God?"*

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እኩይን በሁለት ይመድባሉ። አንደኛው ምግባራዊ እኩይ ሲኾን፣ ሌላኛው ሕማም ነው። የመዠመሪያው በሰው የሚፈጸም ሲኾን፣ ኋለኛው በሰው ላይ የሚፈጸም ነው።[122]

በሰው ላይ የሚደርሰው እኩይ በቅጣትነት እና በፍርድነት ይተረጐማል። በቅጣት የእግዚአብሔር ፍቅር፤ በፍርድ የእግዚአብሔር ፍትሕ ይገለጣል። ቅጣት በወቅቱ የሚያሳዝን በመኾኑ "እኩይ" ተባለ እንጂ ዘለዓለማዊ ፍሬው ሲታይ እጅግ ያማረ ነው። "ቅጣት ኹሉ በወቅቱ የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፤ በኋላ ግን ለለመዱት ሰዎች የጽድቅና የሰላም ፍሬ ያስገኛላቸዋል" እንዲል።[123] ፍርድ ከሚቀበለው ሰው አንፃር "እኩይ" ይባል እንጂ ፍትሐ እግዚአብሔር የሚፈጸምበት መንገድ ነው።

---

[122] St. Augustine, De Libero Arbitrio, Book 1: "We tend to call something evil in two ways: firstly, when someone has done evil; secondly, when someone has suffered something evil."

[123] ዕብ 12፥11

"በየቀኑ በደልና ግፍ ይፈጸማል። ኃጥኡ ተንደላቆ ይኖራል፤ የጻድቁ መከራ ብዙ ነው። እንኪያስ ፍትሐ እግዚአብሔር ከወዴት አለ?" የምትል ወንድሜ፤"ጆሮን የተከለው እርሱ አይሰማምን? ዐይንንስ የሠራ እርሱ አያይምን?"[124] "ሕግ ላልቷል፤ መድሎተ ፍትሕ ተጨበርብሯል" የምትል የቁርጥ ፍርድ ቀን እንዳለ ላሳውቅህ እወዳለሁ! በዚያ ቀን ኹሉን በመለኮታዊ መብራቱ ይፈትሻል፤ ከዓይኑ የሚሰወር የለም።

አሁን የትዕግሥቱን ባለጠግነት ተመልክተህ፣ "የፍትሕ ያለ!" አልህ እንጂ ታላቁ የፍትሕ ቀን በዓይነ ሥጋህ ቢታይህ ልብህ ከጐድን አጥንቶችህ "ልውጣ ልውጣ" ባለች፣ ፍርሃት እስከ ዐጥንትህ ዘልቆ በገባ፣ ከናፍርትህ በድንጋጤ በተንቀጠቀጡ ነበር። ያ ቀን "የመዓት፣ የመከራ፣ የጭንቀት፣ የሁከትና የጥፋት ቀን ነው።"[125]

አንተ፣ "እግዚአብሔር ስለ እኛ ነገር አይገደውም እንጂ ቢገደውስ እንዴት ግፍ ሲፈጸም ይታገሣል?" ትላለህ። በውኑ "እግዚአብሔር ሩኅሩኅ ቸር አምላክ፣ ለቁጣ የዘገየ፣ ፍቅሩና ታማኝነቱ የበዛ" [126] መኾኑ ሊያስመሰግነው እንጂ ሊወቀስበት ይገባል? ምሕረቱን የምታቃልል በገዛ ራስህ ላይ ጥፋትን እንደምታመጣ አታውቅምን? ይህም ከእኛው ባለቅኔዎች አንዱ፣ "ውረድ ወይ ፍረድ!" ይሉታል እግዚአብሔርን፣ ልባቸው ሲቆስል፤ ቢወርድ ፊቱ ቆመው የሚያዩት ይመስል፤ ቢፈርድ የሚተርፉ የሚጸድቁ ይመስል" እንዳለው ነው። እግዚአብሔር እንደ ሥራችን ቢፈርድብን ኖሮ ከምድረ ገጽ በተደመሰስን፣ ሥጋችን ወደ ከርሰ ምድር፣ ነፍሳችን ወደ ሲዖል በተጣለ ነበር።

"እግዚአብሔር ለቁጣ የዘገየ" ቢኾንም፣ "በደለኛውን ሳይቀጣ አያልፍም። "[127] በደለኛውን በሚቀጣ ጊዜ "ቁጣውን ማን ሊቋቋም ይችላል? መዓቱ እንደ እሳት ይፈሳል። በአምላክ ዘንድ አድሏዊነት የለም"፤ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው

[124] መዝ 94፡7-9

[125] ሶፎ 1፡15

[126] ዘጸ34፡6

[127] ናሆም 1፡3

መጠን ይከፍለዋል።[128] እንኪያስ ወንድሜ አንባቢ ኾይ፤ መዓትም ምሕረትም በእግዚአብሔር እጅ መኾኑን ተረድተኽ ምሕረቱን ምረጥ። እግዚአብሔር ለአድኖተ ዓለም የዘረጋው የምሕረት እጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የዘረጋልንን ወርቃማ የጸጋ ዘንግ ብንቃወም፣ ሰይፈ መዓቱ ያጠፋናል።

ሰው ክፉን በመውደድ፣ የማይገባውን በመምረጥ የእግዚአብሔርን ሥልጣን ተጋፋ። የእግዚአብሔርን አምላካዊ ፍቃድ ከማገልገል፣ በራሱ ፍቃድ መኖር መረጠ። በዚህም የውድቀት ምዕራፍ ጀመረ። ኀጢአት አዳምን እና ሔዋንን ከእግዚአብሔር ለያቸው። ከእግዚአብሔር መለየታቸው ደግሞ የችግራቸው፣ የፍዳቸውና የመርገማቸው ሁሉ መነሻ ምንጭ ነው። ከውብ መኖርያቸው መፈናቀል፣ የባሕርያቸው ጉስቁልና አሉታዊ ፍርሃታቸው ሁሉ የዚህ ውድቀት ክትያ[129] ነው። እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ እነርሱን መስለውና አክለው የሚወለዱ ልጆቻቸው ሁሉ የውድቀታቸው፣ የበደላቸው፣ የብክለታቸው እና የቅጣታቸው ተካፋይ ናቸው። ከባሕሪው መጎስቀል የተነሣ ሁሉ ጽድቅን ማድረግ የተሳነው (ምውት)፣ ሥጋዊ፣ የአጋንንት መጠቀሚያ መሣርያ፤ የእግዚአብሔር ጠላት ሆነ።[130] በባሕርይ "አምሳለ ሥላሴ" ቢኾንም፣ በግብር መላእከ ጽልመትንና የዱር አውሬ መሰለ። በዚኽም ከመዓረጉ ወርዶ የዲያብሎስ የግብር ልጅ ኾነ። ብክለት የአዳም ልጆች ሁሉ የባሕርይ ገንዘባቸው በመሆኑ ከአዳም ከወረሱት ኀጢአት ሌላ የግልና የቡድን ኀጢአት በመጨመር የሰው ልጆች በደልና ዓመፅ በየጊዜው እየበዛና እያደገ ሄደ።

ሰው ሆይ፤ እኩይ የፍቃድህ ውሉድ፣ የውዴታህ ፍሬ እንደኾነ አስተውል! የማይገባህን መርጠህ የእግዚአብሔርን ሥልጣን ተጋፍተህ ጉስቁልናን፣ መርገምን፣ ፍዳንና ኩነኔን በራስህ ላይ ያመጣክ አንተው መኾንህን እወቅ! ከራስህ ርቀህ የእኩይን መንስኤ ብትፈልግ በከንቱ ትደክማለኽ።

---

[128] ናሆም 1፡6

[129] መዘዝ፣ ውጤት

[130] ኤፌ 2፡1-3

*"Do not then go beyond yourself to seek for evil... Each of us, let us acknowledge it, is the first author of his own vice. Do not look for the guiding cause beyond yourself, but recognise that evil, rightly so called, has no other origin than our voluntary falls. "*[131]

[131] St. Basil, The Hexaemeron, Homily 2, 5

# ጥያቄ

ዜና ፍጥረት ሲነገር በአእምሮ ውስጥ የማይርመሰመስ የጥያቄ ዓይነት የለም። ከሕፃኑ የሰንበት ተማሪ እስከ በሳሉ ምሁር ድረስ ኹሉ በጥያቄ ይሞላል። በዚህ ክፍል ዜና ፍጥረት ሲነገር ከሚነሱ ጥያቄዎች መካከል አንዱን እንመለከታለን።

እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ከመፍጠሩ በፊት የት ነበር?

አንድ አባት እንዲኽ ዓይነት ጥያቄ ቀርቦላቸው፣ "እንዲህ ያለ ጥያቄ ለሚጠይቁ ገሃነምን እያሰናዳ ነበር" ሲሉ መልሰዋል።[132] በእርግጥ በተቃርኖ መንፈስ መለኮታዊ ምሥጢራትን የሚመረምሩ ተግሣጽ ማስጠንቀቂያ ይገባቸዋል። ኾኖም በትሁት መንፈስ ለሚጠይቁን በተረዳን መጠን የመመለስ የፍቅር ግዴታ አለብን። መሳቂያ መሳለቂያ ልናደርጋቸው አይገባም።

---

[132] St. Augustine, The confessions, Book 11, Chap. 12

# ስፍራ

እግዚአብሔር አካል[133] ወይም የአካል ክፍሎች የሉትም።[134] አካል በስፍራ እንደሚገኝ፣ እግዚአብሔር በስፍራ አይገኝም። በተቃራኒው ስፍራ ኹሉ በእርሱ ይገኛል እንጂ። "ስፍራ ሁሉ በእርሱ ይገኛል" ማለታችን፡- "የስፍራ ሁሉ መገኛ፣ አባት፣ ፈጣሪ ነው" ለማለት እንጂ እርሱ ስፍራ ሆኖ፣ ስፍራ እንደ አካል በእርሱ ስለሚገኝ አይደለም።

"እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ከመፍጠሩ በፊት የት ነበር?" ብሎ ለሚጠይቅ፡- መልሳችን "እግዚአብሔር አካል የለውም፤ በስፍራ አይወሰንም" የሚል ነው። መገኘቱ በስፍራ ያይደል ረቂቅ በኾነ መለኮታዊ ህልውና ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ እግዚአብሔር ቢሆንም ተደራሲያኑ ግን ሰዎች ነን። ስለዚህ ለአቅመ ልቡናችን አማጥኖ ራሱን በሰብዓዊ ቋንቋ ገልጧል። ብርሃነ መለኮቱን ብዙ መሸፈኛ አከናንቦ ለዕይታችን ባያቀርብ፣ በንጹሕ ጨረሮቹ በታወርን ነበር። ቅዱሳት መጽሐፍት በሰው ልጆች ልሳን ይናገራሉ።[135] በቅዱሳት መጽሐፍት አካል ወይም የአካል ክፍሎች የሌሉት አምላክ ራሱን በአካለ ሰብዓዊ[136]

---

[133] Body, not person

[134] Origen, De Principiis, Book 1: "God, therefore, is not to be thought of as being either a body or as existing in a body." "John, in his Gospel, when asserting that "no one hath seen God at any time," manifestly declares to all who are capable of understanding, that there is no nature to which God is visible: not as if, He were a being who was visible by nature, and merely escaped or baffled the view of a frailer creature, but because by the nature of His being it is impossible for Him to be seen."

Thomas Aquines, Summa Theologiae, Part 1, Q, 3: "It is absolutely true that God is not a body."

[135] Babylonian Talmud, Yebamoth, 71a

[136] Anthropomorphic language

ቋንቋ ገልጧል። ራሱን በሰብዓዊ ቋንቋ ቢገልጥልን ሰው አድርገን ልናየው አይገባም።

"አምላክ እንደ ሰው አካልና የአካል ክፍሎች አሉት" የሚሉ አካለሰብዓውያን [137] ይባላሉ። እሊህ "እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ፈጥሮታልና አምላክ በአካል ሰውን ይመስላል" ባዮች ናቸው።[138] በእርግጥ ሰው "በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠረ" ማለት በተክለ ሰውነት እግዚአብሔርን ይመስላል ማለት ነውን? ከግንዱ የተለየ ቅርንጫፍ ሕያውነቱን እንደሚያጣ፣ ከምንባቡ የተነጠለ ጥቅስ ለዛውን ስለሚያጣ ጥቅሶች ከምንባባቸው ጋር ተገናዝበው መተርጐም አለባቸው። ኃይለ ቃሉ እነሆ! እግዚአብሔር፣ "ሰውን በመልካችን፣ በአምሳላችን እንሥራ፤ በባሕር ዓሦች፣ በሰማይ ወፎች፣ በከብቶች፣ በምድር ሁሉ ላይ፣ እንዲሁም በምድርም በሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው" አለ። [139] "በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠረ" ቢባል፦ በገዢነት ስለሚመስለው እንጂ በአካል መስሎትስ አይደለም። በጌትነት ጌታውን መስሎ ሥነ ፍጥረታትን ይገዛል። በሰው ላይ የተገለጠው የእግዚአብሔር መልክ (Imago Dei) ጌትነት ነው።[140]

"የእግዚአብሔር ፊት"፣[141] "የእግዚአብሔር ዐይኖች"[142] "የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ"[143] በዙፋን ላይ መቀመጡን፣[144] መነሣቱን፣[145] ...ወዘተ እኒህን እና

---

[137] Anthropomorphites

[138] Moses Maimonides, The Guide of the Perplexed, Part 1, Chap. 1: "People have thought that in the Hebrew language image denotes the shape and configuration of a thing. This supposition led them to the pure doctrine of the corporeality of God, on account of His saying: Let us make man in our image, after our likeness. For they thought that God has a man's form, I mean his shape and configuration."

[139] ዘፍ 1፡26

[140] Thomas Aquinas, Summa Theologiae, Part 1, Q3: "Man is said to be after the image of God, not as regards his body, but as regards that where by he excels other animals."

Moses Maimonides, The Guide of the Perplexed, Part 1, Chap. 1: "That which was meant in the scriptural dictum, Let us make man in our image, was the specific form, which is intellectual apprehension, not the shape and configuration."

[141] መዝ 34፡16

የመሰሰሉ ምንባባትን እየጠቀሱ፣ “እግዚአብሔር አካልና የአካል ክፍሎች አሉት” ይላሉ። ስህተታቸው ለምሳሌያዊ ምንባባት ፊደላዊ ትርጓሜ መስጠታቸው ነው። ይህም የአተረጓጐም ክህሎታቸው አለመጐልበቱን ያመላክታል። “ልጅ ምሳሌያዊውን ከፊደላዊው መለየት ይሳነዋል” እንዲል አፍላጡን።[146] ምሳሌያዊ ምንባባት በፊደል አንድ ነገር ይላሉ፤ በትርጓሜ ሌላ ነገር ያመለክታሉ። ቅዱሳት መጽሐፍት ለእግዚአብሔር አካልና የአካል ክፍሎች ሰጥተው ቢናገሩ ለእኛ መረዳት አማጥነው እንጂ እግዚአብሔር አካልና የአካል ክፍሎች ኖረውትስ አይደለም።

ቅዱሳት መጽሐፍት “አየ፣ ተመለከተ” ቢሉ፣ አዋቂነቱን ለማመልከት እንጂ ዓይነ ሥጋ ኖሮትስ አይደለም።[147] ጌትነት ሥልጣኑን በመንበር በበትር መስለው ይናገራሉ እንጂ የሚቀመጥ በትር የሚይዝ ኾኖስ አይደለም። አንድ ነገር ሊያደርግ የቆረጠ ሰው በመነሣት እንቅስቃሴ እንደሚጀምር፣ “እግዚአብሔር ተነሣ” ቢባል ሥራውን የሚፈጽምበት ጊዜ መሆኑን ለማመልከት እንጂ የሚቆም የሚቀመጥ ኾኖስ አይደለም።

ወንድሜ አንባቢ ኾይ፤ እግዚአብሔር አካልና የአካል ክፍሎች እንደሌሉት ከሁለተኛይቱን ቃል ተረዳ። ሁለተኛይቱን ቃል ““በላይ በሰማይ ወይም በታች በምድር ካለው ወይም በውሃ ውስጥ ከሚኖሩት ነገሮች በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ” የምትል ናት። ““በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ” ለምን ተባለ?” ቢባል፡- እግዚአብሔር አካል ስለሌለው በርዝመት፣ በስፋትና በከፍታው ስለማይወሰን ነው። መጠን፣ ቅርጽ፣ ክብደት፣ ቀለም

---

142 2ዜና 16፡9

143 መዝ 118፡16

144 ኢሳ 6፡1

145 መዝ 12፡5 ኢሳ 33፡10

146 Plato, The Republic, Book 2

147 Thomas Aquinas, Summa Theologiae, Part 1, Q3: “The act of the eye is to see hence the eyes attributed to God signifies His power of seeing intellectually, not sensibly.

Moses Maimonides, The Guide of the Perplexed, Part 1, Chap. 4: “All this refers to intellectual apprehension and in no way to the eye's seeing, as the eye can only apprehend a body... ”

የለውም። እግዚአብሔር አካል አለው የሚሉ ኢ-ውሱንነቱን ይክዳሉ።[148] እንኪያስ ቅርጽና መልክ ሰጥቶ በምስል እግዚአብሔርን ለሰው ዕይታ ሊያቀርብ የሚችል ማን ነው? ቅዱስ ኢሳይያስ “እግዚአብሔርን… ከየትኛው ምስል ጋር ታነጻጽሩታላችሁ?” ሲል ይጠይቃል። ይህን ለማድረግ የሚሞክሩ ሁለተኛይቱን ቃል ይተላለፋሉ።[149]

ቤተ መቅደሱን የተመለከተ፣ “እግዚአብሔር በስፍራ ተወስኖ ይኖራል” ብሎ እንዳያስብ፣ “ለስሜ ቤት የሚሠራልኝ እርሱ ነው”[150] የተባለ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት፣ የመዠመሪያውን ቤተ መቅደስ ሠርቶ ባስመረቀ ጊዜ፣ “በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ፤ ሰማያትና ሰማየ ሰማያት እንኳ አንተን ሊይዙህ አይችሉም፤ ታዲያ እኔ የሠራሁት ይህ ቤተ መቅደስማ ምንኛ ያንስ!”[151] ሲል እግዚአብሔር በስፍራ እንደማይወሰን አስረድቷል። ምሉዕ በኩለሄ እግዚአብሔር ራሱ በነቢዩ ኢሳይያስ አድሮ፣ “ሰማይ መንበሬ ነው፤ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዓይነት ነው? የማርፍበትስ ስፍራ ምንድር ነው?” ሲል በንጉሥ ሰሎሞን አድሮ የተናገረውን አጽንቷል።[152] ቅዱስ ጳውሎስም ከአባቶቹ ከነቢያት፣ ከወንድሞቹ ከሐዋርያት ጋር በአንድ ልብ መካሪነት፣ በአንድ ቃል ተናጋሪነት፣ “ዓለምንና በውስጡ ያለውን ኹሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነው፤ ስለዚህም እርሱ የሰው እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም”[153] ብሏል። ምስክር እንዲኾኑ እኒ ሦስቱን አቀረብን እንጂ ቅዱሳት መጽሐፍት በየገጻቸው ይኽንን የሚናገሩ አይደሉምን?

---

[148] St. John of Damascus, The Orthodox Faith, Book 1, Chap.1: “For how could that possess body which is infinite, and boundless, and formless, and intangible and invisible, in short, simple and not compound?”

[149] Catechism of the Catholic Church, Part 3, sect. 2, Catechism of the Council of Trent, Part 3

[150] 1ዜና 22፡10

[151] 2ዜና 6፡18

[152] ኢሳ 66፡1

[153] ሐዋ 17፡24

"እግዚአብሔር ምንድን ነው? መገኘቱስ እንዴት ያለ ነው?" ቢሉ፦ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ መገኘቱ ስፍራ በመያዝ ያይደል ረቂቅ በኾነ መለኮታዊ ሕልውና ነው።[154] እርሱ መንበር የማይችለው፣ ቤት የማይወስነው ነው። እርሱን ለማምለክ ስፍራ የሚመርጡ አያውቁትም። ጌታችን እንዲህ ያሉትን በመቃወም፣ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው"[155] ይላል። እግዚአብሔር ምሉዕ በኩለሄ[156] ነው፤ በሰማይ በምድርም ምሉዕ ነው። መለኮት ሰማይና ምድርን ይወስናል እንጂ አይወሰንም።

ጌታችን "በዚህ ተራራም ሆነ በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ እንደሚመጣ እመኝኝ.. አሁንም መጥቶአል"[157] ባለው መሠረት፣ በዘመነ ሐዲስ ከምሉዕ በኩለሄነቱ ጋር በሚራከብ መልኩ፣ በኹሉ ስፍራ ይሰገድለታል። እርሱን ለሚያመልኩ መላለሙ ቤተ መቅደስ ነው፤ ለእርሱ ለሚኖሩ መላለሙ ገዳም ነው፤ ወደ እርሱ ለሚጸልዩ መላለሙ መሠዊያ ነው። ሊቀ ሐዋርያት፣ ቅዱስ ጳውሎስ፣ "ወንድሞች በሁሉም ስፍራ… እንዲጸልዩ እፈልጋለሁ"[158] እንዲል።

በአካላዊ እጅ ያይደል በመለኮታዊ መግቦቱ ዓለምን የያዘ ማን አለ? በአካላዊ ምላስ፣ አየር ላይ በሚፈስ ቃል፣ ተሰምቶ በሚያልፍ ድምጽ ያይደል ለልብ የሚናገር ማን አለ? ያለእግር የሚጠፉትን ለማዳን የሚገሰግስ ማን አለ?

---

[154] St. Augustine, Eighty Three different questions, Q, 20
[155] ዮሐ 4፡24
[156] በሁሉ ቦታ የሚገኝ
[157] ዮሐ 4፡21-23
[158] 1ጢሞ 2፡8

# ጊዜ

“እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ከመፍጠሩ በፊት የት ነበር?“ የሚለው ጥያቄ ሌላም ችግር አለበት። ስፍራና ጊዜ (Space-Time) አንድ ላይ ካለ መኾን ወደ መኾን የመጡ ናቸው። ሰማይንና ምድር ከመፈጠራቸው በፊት ያለፈ ጊዜ የለም።[159] እንኪያስ “ሰማይንና ምድርን ከመፍጠሩ በፊት“ በማለት የትኛውን ጊዜ ልናመለክት እንችላለን?[160]

“የእግዚአብሔር አኗኗር እንዴት ያለ ነው?“ ቢባል፡- በስፍራ የማይወሰን መንፈስ፣ በጊዜ ውስጥ የማይኖር ዘለዓለማዊ ነው። እርሱ በጊዜ መተካከል ውስጥ የሚኖር አይደለም። በእርሱ ዘንድ ያለፈና የሚመጣ ጊዜ የለም። “ጊዜ የምንጓዝበት ቀጥተኛ መስመር ቢኾን፣ እግዚአብሔር ይህ መስመር የተሰመረበት ገጽ ነው“ እንዳል ሲ.ኤስ. ሊዊስ።

“እግዚአብሔር ጊዜ ከፈጠረ በኋላ እንደ እኛ በጊዜ ርምደት ውስጥ ካለፈው ወደሚመጣው የሚጓዝ ኾኖ ተለውጧል“ የሚሉ፣ የእግዚአብሔርን

---

[159] St. Augustine, Two Books on Genesis; Against the Manichees, Book 1, Chap. 2: “For God also made time, and thus there was no time before he made time. Hence, we cannot say that there was a time when God had not yet made anything. For how could there be a time that God had not made since he is the maker of all time?”

Philo, De Opificio Mundi, Sect. 7: “… time there was not before there was a world.”

[160] St. Augustine, Two Books on Genesis; Against the Manichees, Book 1, Chap. 2: ” time is not eternal in the same way that God is eternal, because God who is the maker of time is before time.”

St. Augustine, The confessions, Book 11, Chap. 13: “Thou hast made all time; and before all times Thou art, nor in any time was there not time.” Chap. 30: “God, the eternal creator of all times, art before all times, and that no times are co-eternal with Thee.”

ካለ ሰብዓዊ ሥነ መለኮት በተቃራኒው አምላክን የጊዜ እስረኛ ያደርጋል። ብዙዎች እንዲህ ባለው ስህተት ውስጥ ይገኛሉ።

አይለወጤነት የዘነጉ ናቸው። ወንድሜ አንባቢ ኾይ፤ የእግዚአብሔር አይለወጤነት ለድርድር ከማይቀርቡ የሃይማኖት አናቅጽት አንዱ እንደኾነ ላስታውስህ እወዳለሁ! እግዚአብሔር ተለወጠ ብለን በሕሊናችን አናስብም፣ በቃላችን አንናገርም።

አንተ፣ "በጊዜ ውስጥ ሳይኖር በጊዜ ውስጥ ከሚኾነው ጋር እንዴት ይገናኛል?" ትላለህ። እኔም ልጠይቅህ፦ መለኮት በስፍራ ሳይወሰን በኹሉ ስፍራ ከተገኘ፣ በጊዜ ሳይወሰን ጊዜያት ኹሉ በፊቱ ቢገኙ ድንቁ ብርቁ ምንድን ነው? አእምሮህ፣ "ዘለዓለማዊ ኾኖ ከጊዜያውያን ጋር ሕብረት ማድረግ ይሳነዋል" ሲል፣ "ጊዜን ከፈጠረ በኋላ ወደ ጊዜያዊነት ተለወጠ" ማለትን መረጠ? ወዳጄ ኾይ፤ በራስህ ማስተዋል መደገፍህ እነ አርዮስ ከወደቁበት የምንፍቅና ጉድጓድ እንዳይጥልህ ፍራ።

"ዘለዓለም ከጊዜ በምን ይለያል?" ቢሉ፦ ጊዜ ይተካካል። ያለፈው ጊዜ ሄዷል፤ ከእንግዲህ የለም። የሚመጣውን ጊዜ ገና አላገኘነውም። አሁን ያለችው አሁን ብቻ ናት፤ እርሷም ከወራጅ ውኃ በሚልቅ ፍጥነት የምታልፍ ናት። አሁን ቅድምን አባራ የቅድምን ቦታ ይዛለች። በኋላ ይመጣና አሁንን አባሮ ስፍራዋን ይይዛል። በዘለዓለም ዘንድ እንዲህ ያለ መተካካት የለም። ያለፈና የሚመጣ ጊዜ የለም። በዘለዓለም ያለው ቅድምን ያልተካ፣ በኋላም የማይተካው "ጸንቶ የሚኖር አሁን" ብቻ ነው። "የሚያልፍ አሁን ጊዜን ይሰራል፤ ጸንቶ የሚቆም አሁን ዘለዓለምን ይሰራል" እንዳለ ቦኢትየስ።[161]

> *"Eternity is **the whole, simultaneous, perfect possession of limitless life**, which we can better understand perhaps by comparing it to temporal things. One who lives in time progresses in the present from the past and into the future. There is nothing in time that can embrace the entirety of his*

[161] Boethius, On Trinity, Book 5, Sect. 6: "The now that flows away makes time, the now that stands still makes eternity"

*existence. He has no idea about tomorrow and has already lost his hold on the past. In this day-to-day life, he lives only in the transitory moment. Whatever is in time—even though, as Aristotle says, time had no beginning and has no ending and extends into infi nity—is still not what may correctly be called 'eternal.' Its life may be infinitely long, but still it does not comprehend its entire extent simultaneously. It is still waiting for the future to reveal itself and it has let go of much of the past. What may properly be called eternal is quite different, in that it has knowledge of the whole of life, can see the future, and has lost nothing of the past. It is in* ***an eternal present*** *and has an understanding of the entire flow of time."*[162]

ያለፈው ጊዜ ሄዷል፤ ከእንግዲህ የለም። የሚመጣውን ጊዜ ገና አላገኘነውም። አሁን ያለችው አሁን ብቻ ናት፤ እርሷም ከወራጅ ውኋ በሚልቅ ፍጥነት የምታልፍ ናት። ያለፈው ከአሁን ቀደም ነው፤ ወደፊት ከአሁን በኋላ ነው። ለመሆኑ "አሁን" ድንበሯ ምን ያህል ነው? ግዛተ አፄዋ ከየት እስከ የት ነው? ሙሉ ዓመት በአንድ ላይ አሁን ይባል ዘንድ አይችልም። "ለምን?" ቢባል፡- ወደ ዓመቱ ከመግባታችን በፊት ሙሉ ዓመቱ የወደፊት ጊዜ ነበር። ወደ ዓመቱ ስንገባ የዓመቱ የተወሰነ ክፍል ያለፈ ጊዜ፣ የቀረው ደግሞ የወደፊት ጊዜ ይኾናል። ዓመቱን ስንጨርስ ሙሉ ዓመቱ ያለፈ ጊዜ ይሆናል። እንኪያስ እንዴት ሙሉ ዓመት በአንድ ላይ "አሁን" ይባለል? በተመሳሳይ ምክንያት ሙሉ ወራት፣ ቀናት፣ ሰዓታት፣ ደቂቆች፣ ሴኮንዶችን፣ ደቂቀ ሰኮንዶችም "አሁን" ሊባሉ አይችሉም።

---

162 Boethius, Consolation Of Philosophy, Book 5, Chap 6

“አሁን እንዴት ያለች ናት?” ቢባል፦ “አሁን” ከእርሷ ባነሱ ስፍረ ጊዜያት ልትከፈል የማትችል፣ ያለፈና የሚመጣ ጊዜያት ያልቀላቀለች፣ ንጽዕት ቅፅበት ናት።[163] በቅፅበታዊ ፍጥነት ባለፈውና በሚመጣው መካከል ድንበር ኾና ትጓዛለች። አሁንን ልንይዛት አንችልም። ሥፍራ የምትቀይር፣ ተንቀሳቃሽ ድንበር ናት።[164] በየቅፅበቱ ትታደሳለች። የቅድሟ አሁን፣ አሁን ቅድም ሆናለች። የአሁኗ አሁን፣ ቅድም በኋላ ነበረች። አሁን በኋላዎችን ወደ ራሷ እየቀየረች፣ ራሱዋን ወደ ቅድሞች እየጣለች፣ ከቅድም ወደ በኋላ ትጋልባለች። በኋላዎችም ተሰልፈው አሁን ለመሆን ይጠባበቃሉ። አሁን ሆነው ብቅ ካሉ በኋላ ቅድም ኾነው እልም ይላሉ።

እግዚአብሔር ዘንድ ያለፈና የሚመጣ ጊዜ፣ ትውስታና ግምት የለም። “ለምን?” ቢባል፦ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ነው። በዘለዓለም ያለፈና የሚመጣ ጊዜ የለም። ዳግመኛም ያለፈ ጊዜ በሌለበት ትውስታ፣ የሚመጣ ጊዜ በሌለበት ተስፋ የለም። ጊዜያውያን የኾን እኛ ቀጥተኛ ግንኙነት ያለን ከአሁን ጋር ብቻ ነው። ያለፈው ጊዜ ትውስታ ብቻ አስቀርቶልን ሄዷል፤ የሚመጣውን ጊዜ በግምት ብቻ እናውቀዋለን። ዘለዓለማዊ በኾነ በእርሱ ዘንድ ትውስታን ጥሎልን ያለፈ ጊዜና የሚገመት ወደፊት የለም።

ታላቁ ጎርጎርዮስ በእግዚአብሔር ያለፈና የሚመጣ ጊዜ እንደሌለ እያስረዳ የሚከተለውን ጽፏል፦

> *“Without beginning and without end: where unto neither things gone-by are past, nor things still-to-*

[163] St. Augustine, The confessions, Book 11, Chap. 15: “If any portion of time be conceived which cannot now be divided into even the minutest particles of moments, this only is that which may be called present.”

[164] Paul Tillich, The Eternal now, “The riddle of the present is the deepest of all the riddles of time.”

*come, as though they did not appear, are absent."*[165]

*"A man carries back the eyes of His mind in recollection, and stretches them out before in anticipation, as it were over a space of time, he expands them in imagination."*[166]

ወንድሜ አንባቢ ኾይ፤ ጊዜያዊነታችን በዕውቀታችን ላይ ያለውን አስከትሎት ተመልከት! በጊዜ ርምደት ውስጥ ዕውቀታችን ይለዋወጣል። የማናውቀውን እናውቃለን፤ የምናውቀውን እንረሳለን። ስላለፈው ጊዜ ያለን ዕውቀት ትውስታ ነው። የማስታወስ ዓቅማችን ሲደክምና እየቆየ ሲሄድ የምናውቀውን እንኳን እየረሳን እንሄዳለን።[167] ስለሚመጣው ጊዜ ያለን ዕውቀት ግምት ነው። ቀጥተኛ እውቀት ያለን ስለ አሁን ብቻ ነው። በትውስታ ካልኾነ ቅድምን አናገኝም። በግምት ካልኾነ የሚመጣውን አናውቅም።

እኛ በሚያልፍ አሁን ሆነን እንደምናይ፣ እግዚአብሔር ጸንቶ በሚቆም አሁን ኾኖ ያያል። ያለፈውን ያስታውስ ዘንድ ያለፈ ጊዜ የለውም። የሚመጣውን ይገምት ዘንድ፣ የሚመጣ ጊዜ የለውም። ከፊታችን በፍጥነት እየጋለበ የሸሸን ቅድም፣ በእርሱ ዘንድ በአሁንነት ጸንቶ ይኖራል። ገና ያላገኘነው በኋላ፣ በእርሱ ዘንድ አሁን ኾኖ ተገኝቷል። በትዝታ ወደ ኋላ አይዘርም፤ በግምት ወዳልመጣው አይዘረጋም። ድሮ ሲል የሚያስታውሰው፣ ወደ ፊት ብሎ የሚጠባበቀው የለም። ስለዚህ ጻዲቅ ኢዮብ፣ "አንተ ዐይንህ የሥጋ ለባሽ ዐይን ነውን? ሟች የሆነ የሰው

[165] Gregory The Pope, The Books Of The Morals (Job), Book 9, Sec. 72

[166] Gregory The Pope, The Books Of The Morals (Job), Book 16, Sec. 54

[167] Omnia fert aetas, animum quoque- Time bears away everything, even memory (Virgil)

ልጅ እንደሚያይ ታያለህን? ዘመንህ እንደ ሟች ሰው ዘመን ነውን? ወይስ ዓመታትህ እንደ ሰው ዓመታት ናቸውን?" ይላል።

"እንኪያስ ስለምን ቅዱሳት መጽሐፍት ቅድመ ዕውቀትን ለእግዚአብሔር ሰጥተው ይናገራሉ?" ቢባል፦ ቅዱሳት መጽሐፍት በሰው ልጆች ልሳን ስለሚናገሩ እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለፈና የሚመጣ ጊዜ ኖሮስ አይደለም። የቅድመ ዕውቀት ቅድመ ዕውቀትነቱ ለእግዚአብሔር ሳይኾን ጊዜያውያን ለኾንን ለእኛ ነው። እኛ "ቅድመ እውቀት" ብለን የምጠራው ለእርሱ የአሁን ዕውቀት ነው። ቅድመ ዕውቀቱ በእውነት ላይ የተመሰረተ ዕውቀት እንጂ ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት አይደለም።[168] ጊዜ የሚገልጥለት አንዳች የለም።[169] በዘለዓለማዊ አሁን ውስጥ ኾኖ፦ የነበረ፣ ያለና የሚመጣውን አንድ ላይ ያያል። ለሰው እንደሚያወራ ሰው፣ " የነበረ፣ ያለና የሚመጣ" እንበል እንጂ በእርሱ ዘንድ ኹሉም ያሉ ናቸው።

ኹሉ ጊዜያውያን፣ እግዚአብሔር ብቻውን ዘለዓለማዊ ነው። ዘለዓለማዊ እይታውን የሚጋራ ማን ነው? አምላክ እንደሚያይ ሊያይ የሚችን ማን ነው? ወደፊታችን እንደ አሁናችን ይታየዋል። ቅዱስ ኢሳይያስ፣ ከጊዜ ውጪ ሆኖ ከጊዜ በኋላ ሊሆን ያለውን፣ በጊዜ ውስጥ ባሉ አገልጋዮቹ የሚገልጠውን እውነተኛ አምላክ እያወደሰ፣ የጊዜ ተማሪዎች የሆኑ ጣዖታት ላይ ይሳለቃል።

> *"እኛ እናውቅ ዘንድ ይህን ከመጀመሪያው የተናገረ፣ 'እርሱ ትክክል ነው' እንልም ዘንድ ቀድሞ የተናገረ ማነው? ማንም አልተናገረም፤ ቀደም ብሎ የተናገረ የለም፤ ቃላችሁንም የሰማ የለም። በመጀመሪያ፣ 'እነሆ፤ ተመልከቷቸው' ብዬ ለጽዮን የተናገርሁ እኔ ነበርሁ፤ ለኢየሩሳሌምም የምሥራች ነጋሪን ሰጥቻለሁ።"*[170]

---

[168] Boethius, On Consolation of Philosophy, Book 5: "His foresight is not opinion but knowledge based on truth."

[169] Ibid, Book 5: "He sees what is, what was and what is to come in an instant's insight."

[170] ኢሳ 41፥26 -27

ሐሰተኛ "አማልክት" ተናግረው ባላቸው ዓቅም የተናገሩትን ለመፈጸም ይፍጨረጨራሉ። እግዚአብሔር ግን ሊኾን ያለውን ይገልጣል። "ምሥጢርን የሚገልጥ አምላክ" የምንለውም ከሥነ ፍጥረት የዕውቀት አድማስ ውጪ የሆነውን ገሃድ ስለሚያወጣ ነው። ክርስቲያን ኾይ፤ ሊኾን ያለውን የሚያውቅ እንደ አምላክህ እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም!

"እግዚአብሔር ሊሆን ያለውን ኹሉ የሚያውቅ ከሆነ፣ የሰው ልጅ እግዚአብሔር አስቀድሞ ካወቀው የተለየ ነገር ማድረግ ስለማይችል ነፃ ፍቃድ የለውም። የሰው ልጅ እግዚአብሔር አስቀድሞ ካወቀው የተለየ ነገር ማድረግ ከቻለ፣ የእግዚአብሔር ቅድመ ዕውቀት ሊፋለስ ይችላል"[171] ይህ ያረጀ የፈጀ የሙጉት ነጥብ በዚኽም ዘመን ድኩማንን ማወዛገቡን ቀጥሏል።

አንዳንዶች በዚኽ ተወዛግበው የእግዚአብሔርን ቅድመ ዕውቀት ከመካድ የሰው ልጅን ነፃ ፍቃድ መካድ ይመርጣሉ። እስኪ ልጠይቃችሁ፡- "እግዚአብሔር ሊሆን ያለውን ኹሉ የሚያውቅ ስለኾነ እግዚአብሔር ራሱ አስቀድሞ ካወቀው የተለየ ነገር ማድረግ የማይችል፣ ነፃ ፍቃድ የለውም ማለት ነውን? አስቀድሞ ካወቀው የተለየ ነገር ማድረግ ከቻለ፣ ቅድመ ዕውቀቱ ሊፋለስ ይችላል ማለት ነውን? አንተ ስሁት፤ የሙጉትህን ወጥነት ከጠበክ እንዴት አርጎ ወዳልፈለከው ድምዳሜ እንደሚወስድህ ተመልከት! ለፍጡር ባበጀኸው የብረት ከርቸሌ ፈጣሪን ለማኖር ትገደዳለህ።

አንድ ሰው እየተራመደ ብትመለከት፣ እየተራመደ ስላለ እየተራመደ አየኸው እንጂ አንተ እየተራመደ ስላየኸው አልተራመደም። በተመሳሳይ መልኩ

[171] ምንም እንኳ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ልጆች እንደመከራከሪያ ነጥብ ቢጠቀሙትም ነገርየው ከኢ-አማናዊ ምንጮች የተቀዳ ነው። ነገር ግን ጥንታውያን አበው በአንድ ልብ መካሪነት፣ በአንድ ቃል ተናጋሪነት የሚያወግዙት ነው።

Luther, De Servo Arbitrio: "...He (God) foresees and purposes and does all things by his immutable, eternal, and infallible will. Here is a thunderbolt by which free choice is completely prostrated and shattered, so that those who want free choice asserted must either deny or explain away this thunderbolt, or get rid of it by some other means."

ነገሮች ስለሚፈጸሙ እግዚአብሔር አስቀድሞ አወቃቸው እንጂ እግዚአብሔር አስቀድሞ ስላወቃቸው ነገሮች አይፈጸሙም። ዳግመኛም የቅድመ ዕውቀት ቅድመ ዕውቀትነቱ ለእግዚአብሔር ሳይኾን ጊዜያውያን ለኾንን ለእኛ።

> *"We are by no means compelled, either, retaining the prescience of God, to take away the freedom of the will, or, retaining the freedom of the will, to deny that He is prescient of future things, which is impious.* ***But we embrace both. We faithfully and sincerely confess both. The former, that we may believe well; the latter, that we may live well.****"*[172]

በሌላ ጽንፍ ደግሞ፣ "ነፃ ፍቃድ ስላለኝ ምርጫዬን በመለወጥ የእግዚአብሔርን ቅድመ ዕውቀት አፋልሳለኹ! እግዚአብሔር አስቀድሞ ያየውን ትቼ ሌላ መርጣለኹ!" የሚል ሞኝ ይኖራል። ይህን ብትሞክር እግዚአብሔርን ያይደል ራስህን ታታላለኽ። ምንም ለየት ያለ፣ የማይገመት ነገር ለማድረግ ብትሞክር ከመለኮት ቅድመ ዕውቀት ውጪ ልትሆን አትችልም። የመለኮት ቅድመ ዕውቀት አይፋለስም፤ አይለወጥም።

እግዚአብሔር አይለወጥም። "ለምን" ቢባል፡- እግዚአብሔር በጊዜ መተካከል ውስጥ የሚኖር አይደለም። የጊዜ ፍሰት በሌለበት ደግሞ ለውጥ የለም። ለውጦች ኹሉ በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚከሰቱ በመኾናቸው ጊዜ ቢቆም ለውጥ ይቀራል። ቅዱሳት መጽሐፍ የእግዚአብሔርን አይለወጤነት ከዘለዓለማዊነቱ ጋር አቆራኝተው የሚያስተምሩ አይደሉምን? "ዘመኖቼ እንደ ምሽት ጥላ ናቸው፤ እኔም እንደ ሣር ደርቄአለሁ። እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን ለዘለዓለም በዙፋንህ ተቀምጠሃል።"[173] "ዘመኖቼ እንደ ምሽት ጥላ ናቸው፤ እኔም እንደ ሣር ደርቄአለሁ"

---

[172] St. Augustine, City of God, Book 5, Chap. 10

[173] መዝ 102፡11-12፣ 27

ማለት በጊዜ ፍሰት ውስጥ የምለዋወጥ ጊዜያዊ ፍጥረት ነኝ ከማለት ውጪ ምን ማለት ሊሆን ይችላል? “አንተ ግን ለዘለዓለም በዙፋንህ ተቀምጠሃል” ማለትስ በጊዜ ፍሰት ውስጥ አትለዋወጥም ከማለት ውጪ ምን ማለት ሊሆን ይችላል? በዚያው ምንባብ “አንተ ግን ያው አንተ ነህ፤ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም” ሲል አይለወጤነቱን ከዘለዓለማዊነቱ ጋር ያቆራኛል። ዓመቶቹ የሚተካኩ አይደሉም። ከዚህም የተነሣ እርሱ ያው እርሱ ነው፤ የጊዜ ፍሰት አይቀይረውም።

“ያለፈው ከእንግዲህ የለም፤ የሚመጣው አልተገኘም፤ አሁንም ከወራጅ ውኃ በሚልቅ ፍጥነት የምታልፍ ናት። የጊዜ ባሕርይ እንዲህ ያለ አይደለምን? የጊዜያውያን ፍጥረታትም ባሕርይ እንዲሁ ነው። ያለ እረፍት፣ ያለ ምንም ዓይነት መረጋጋት እንዲጠፉ ተወስኖባቸዋል።“ [174] ጽኑ ብለን የምናስባቸውን ጊዜ ይለውጣቸዋል። እግዚአብሔር ግን ጊዜያትን ይለውጣል እንጂ በጊዜያት አይለወጥም። “ለምን” ቢባል፡- እርሱ የጊዜ ፈጣሪና ገዢ ነው።

በቅዱሳት መጽሐፍት ዘለዓለማዊ አምላክ ራሱን በጊዜያዊ ቋንቋ ገልጧል። ጊዜያውያን ለኾን ለእኛ ራሱን በጊዜያዊ ቋንቋ ቢገልጥልን ጊዜያዊ አድርገን ልናየው አይገባም።

> “As God, although incorporeal, is named in scripture metaphorically by corporeal name, so eternity though simultaneously whole, is called by names implying time and succession.” [175]

[174] St. Basil, The Hexaemeron, Homily 1
Tempus edax rerum
Tempus rerum imperator
[175] Thomas Aquinas, Summa Theologiae, Part 1, Q.10

በጊዜ ፍሰት ወደ ፍጻሜያችን እየገሰገስን፣ ወደ ምድራዊ ቆይታችን ማብቂያን እየተቃረብን ነው። ብዙዎች በቅርብ የሚመጣውን[176] እንጠባበቃለን፤ ፍጻሜያችንን ግን ልናስብ አንወድም። ፍጻሜያችንን ስናስብ ባዶነት ይሰማናል። ከዚኽ ተስፋ መቁረጥ ለማምለጥ፣ “በአሁንና በፍጻሜያችንን መካከል ረጅም ጊዜ ይኖረናል” የሚል ተስፋ እንሰንቃለን። የሚኖረንን ጊዜም በክብር፣ በሀብት፣ ሥጋዊ ምኞትን በመፈጸም ልናጣጥም እንሞክራለን። ይኽም ራስን ማታለል ነው።

[176] Immediate Future

# ዋቢ መጽሐፍት


**Ambrose of Milan**

*The Fathers of the Church, v. 42: Hexameron, Paradise, and Cain and Abel*. Trans. by John J. Savage. Washington, DC: The Catholic University of America Press,1977.

*On Abrahanm*. Trans. by Theodosia Tomkinson. Etna, CA: Center for Traditional Orthodox Studies, 2000.

**Aquinas, Thomas**

*Summa Contra Gentiles, Book 2: On Creation.* Trans. by James F. Anderson. New York, Gaden City: A divion of Doubleday & Company, Inc. 1956.

*Compendium of Theology*. Trans. by Richard J. Regan. Alton Street, Oxford: Oxford University Press, 2009.

**Augustine of Hippo**

*Confessions*. Trans. by Garry Wills. New York: Penguin Books, 2006.

*The City of God (De civitate Dei)*. Trans. by John Healey. 2 vols. London: Dent; New York: Dutton, 1967.

*On Christian Doctrine*. Trans. by D.W. Robertson. New York: Macmillan, 1987.

*The Fathers of the Church, v. 84: On Genesis: Two Books on Genesis against the Manichees; and, On the Literal Interpretation of Genesis, an Unfinished Book*. Trans. by Roland J. Teske. Washington, DC: The Catholic University of America Press, 1991.

*The Trinity.* Trans. by Stephen McKenna. The Fathers of the Church, v. 45. Washington, DC: The Catholic University of America Press,1970.

*Enchiridion,* or, Manual to Laurentius concerning Faith, Hope, and Charity Trans. by Ernest Evans. London: S.P.C.K., 1953.

Hugh of saint Victor, *On the Sacraments of the Christian Faith*. Trans. by Roy J. Deferrari. Mediaeval Academy of America, 58. Cambridge, MA Mediaeval Academy of America, 1951.

*The Fathers of the Church, vol. 74: "St. John Chrysostom, Homilies on Genesis, I—17*" Trans. by Robert C. Hill, Washington D.C: The Catholic University ofAmerica Press, 1986

**Basil the Great**

*The Hexaemeron*. Trans. by Paul A. Boer. Veritatis Splendor Publications, 2012.

**Bede, The Venerable**

*On Genesis*. Trans. by Calvin B. Kendall. Cambridge, Liverpool: Liverpool University Press, 2008.

**Boethius**

*The Consolation of Philosophy*. Trans. by David R. Slavitt. Cambridge, Massachusetts: Harvard University Press, 2008.

**Didymus the Blind**

*The Fathers of the Church: Commentary on Genesis.* Trans. by Robert C. Hill, Washington D.C: The Catholic University of America Press, 2016.

**Hugh, of Saint Victor**

*On the Sacrament of the Christian faith*. Trans. by Roy J. Deferrari. Cambridge, MA: Mediaeval Academy of America, 1951.

**Ibn Ezra, Abraham**

*Midrashim on Bereshit*. Trans. by H. Norman Strickman and Arthur M. Silver. New York: Menorah Publishing Company, Inc., 1940.

**John of Damascus**,

*The Orthodox Faith*. Trans. by Frederick H. Chase, New York: Fathers of the church, inc., 1958

**Lombard, Peter**

*The Sentences, Book 2: On Creation*. Trans. by Giulio Silano. Toronto, Canada: Pontifical Institute of Mediaeval Studies, 2010.

**Maimonides, Moses**

*The Guide of the Perplexed Volume 1.* Trans. by Shlomo Pines. Chicago: The University of Chicago Press, 1963.

*The Guide of the Perplexed Volume 2*. Trans. by Shlomo Pines. Chicago: The University of Chicago Press, 1963.

**Origen**

*The Fathers of the Church, Volume 71: Homilies On Genesis And Exodus* Trans. by Onald E. Heine. Washington, DC: The Catholic University of America Press, 2002.

*On First Principles, Volume 1.* Trans. by John Behr. Alton Street, Oxford: Oxford University Press, 2017.

**Philo of Alexanderia**

*Philo in Ten Volumes, V1: De Opificio Mundi and Legum Allegoria.* Trans. by F.H. Colson and G.H. Whitaker. Cambridge, Massachusetts: Harvard University Press, 1981.

*Philo in Ten Volumes, V7: De Decalogo and De Specialibus Legibus.* Trans. by F.H. Colson. Cambridge, Massachusetts: Harvard University Press, 1998.